# እንድ አዲስ ዘመን

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 275 ሰኔ 5 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




# በ5 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የተገነባው የታዳሽ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ተመረቀ

## -ኢንዱስትሪው ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ለማሸጋገር የጎላ ድርሻ እንደሚኖረው ተገልጿል
## - ኢንዱስትሪው ለማህበራዊ አገልግሎት የ15 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አድርጓል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በ5 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የተገነባው የታዳሽ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ተመረቀ። ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ለማሸጋገር እንደ ታዳሽ ያሉ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች የጎላ ድርሻ እንደሚኖራቸው ተገለጸ።

በኦሮሚያ ክልል ዱከም ከተማ በ5 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የተገነባው የታዳሽ ብረታብረት ኢንዱስትሪ ግንባታው ተጠናቆ ትናንት በተመረቀበት ወቅት የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ እንደገለጹት፤አገር የሚገነቡት፣ የሚያጸኑትና የሚያሻግሩት እንደ አቶ ክብሩይስፋ ያሉ የተግባር ሰዎች ናቸው።በ5 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ወጪ አድርገው ታዳሽ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ገንብተዋል።ኢንዱስትሪው ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ለማሸጋገር የጎላ ድርሻ ይኖረዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ከትንሽ ነገር ተነስቶ ሕይወትን ማሸነፍና ለትውልድ የሚሻገር ሥራ መስራት

በ5 ነጥብ 8 ቢሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሁሉንም ርብርብ የሚሻው የተፈናቃዮች ጉዳይ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሼኽ መሐመድ በሽር ይባላሉ። ተወልደው ባደጉባት እንዲሁም እስከ እርጅና ዘመናቸው በኖሩባት በራህሌ አንቱ የተባሉ ባለፀጋ ነበሩ። በርካታ ቁጥር ያላቸው ግመሎች፣ ፍየሎችና በጎች እንደነበራቸው ይናገራሉ። ከሦስት መቶ በላይ ዘመናዊና ባሕላዊ የንብ ቀፎዎችም ነበራቸው። የንግድ ፍቃድ አውጥተው ወደ ጅቡቲና ሳውዲ ዓረቢያ ማር ይልኩ ነበር። ከዚሁ ንግድ በሚያገኙት ገቢም ከ15 በላይ የሚሆኑ የቤተሰብ አባላቶቻቸውን ያስተዳድሩ ነበር።

አሁን ግን ያ ሁሉ ቀረና በአፋር ክልል ጉያህ በምትባል ቦታ ባለችው የተፈናቃዮች መጠለያ ካምፕ ውስጥ መኖር ከጀመሩ አምስት ወራት ተቆጥረዋል። ሼኽ መሐመድ ብቻም ሳይሆኑ የሕወሓት የሽብር ቡድን ወረራ በፈጸመባቸው የአፋር ወረዳዎች የሚኖሩ በርካታ ዜጎች ተፈናቅለው በክልሉ ውስጥ በሚገኙ 17 ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ተጠልለው ኑሯቸውን በእለት ደራሽ እርዳታ በመምራት ላይ ይገኛሉ።

ከአፋር ክልል የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የሕወሓት የሽብር ቡድኑ በአፋር ክልል ሦስት ጊዜ ወረራ የፈጸመ ሲሆን በእነዚህ ወረራዎች 21 ወረዳዎች ተጎድተዋል። በዚህም ሕጻናትና እናቶች ጨምሮ በርካታ ንጹሃን ዜጎች ሞተዋል፤ የግለሰብ ቤቶችና የንግድ ድርጅቶች ወድመዋል፤ አጠቃላይ በክልሉ ከ20 እስከ 25 ቢሊየን ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል።

የሁሉም ርብርብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ሼኽ መሐመድ በሽር



አቶ መሐመድ ሁሴን የአፋር ክልል የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ፅሕፈት ቤት ኃላፊ



አቶ መሐመድ ሙሳ



ወሮ ዘምዘም ናጂ



# “ሽብርተኝነትን በመዋጋት መንግሥትና ሕዝብ ትኩረታቸውን ወደልማት እንዲመልሱ የሚያስችል ሁኔታ እንፈጥራለን”

## - አቶ ተመስገን ጥሩነህ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ሽብርተኝነትን አጥብቀን በመዋጋት መንግሥትና ሕዝብ ትኩረታቸውን ሙሉ በሙሉ ወደ ሰላምና ወደ ልማት እንዲመልሱ የሚያስችል ሁኔታ እንፈጥራለን ሲሉ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተመስገን ጥሩነህ ተናገሩ።

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተመስገን ጥሩነህ “ሽብርተኝነትን በመከላከል

“ሽብርተኝነትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በክልሉ በሳምንት በአማካኝ ከ8 ሺ እስከ 9 ሺ ሰዎች በወባ በሽታ እየተያዙ ነው

ገጽ 4







# መንግሥት ለ2015ዓ.ም በጀት ከመመደብ ባሻገር በጀቱ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል እንዳለበት ተገለጸ

መዓዛ ማሞ

መንግሥት ለ2015ዓ.ም በጀት ከመመደብ ባሻገር በጀቱ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን መከታተል እንዳለበት የኢኮኖሚ ባለሙያውና የፖሊሲ አማካሪው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ ገለጹ።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት በጀት ለክልሎች እና ለተለያዩ ሥራዎች ከተመደበ በኋላ ምን እየተሰራበት እንደሆነና በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን መከታተል ይገባል።

የተጀመሩ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን ለመጨረስ፣ የምግብ እርዳታ ለሚፈልጉ ወገኖቻችን ለመድረስ፣ በጦርነቱ ምክንያት የፈራረሱ አካባቢዎችን እንደገና ለመገንባት የተመደበውን በጀት በአግባቡ መጠቀም በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በጀቱ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን መቆጣጠር ያስፈልጋል።

ባለፉት ዓመታት እንደ ትልቅ ችግር የታየውን የበጀት ብክነትን መቀነስ ያስፈልጋል። ትልቅ ስራ የሚሰራው ወረዳ ላይ እንደሆነ አስታውሰው ወረዳ ያለው አስተዳደር በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክሮ ስራውን የሚሰራበት መንገድ መኖር እንዳለበት ጠቁመዋል።

መንግሥት በአዲሱ በጀት ዓመት ለረዥም ጊዜ የቆየውን የነዳጅ ድጎማ ማንሳቱ ለኢኮኖሚው መልካም መሆኑን የጠቆሙት የፖሊሲ አማካሪው የጊዜ ገደብ የሌለው ድጎማ ለኢኮኖሚው ጠንቅ መሆኑን ገልጸዋል። ህዝቦች የኢኮኖሚ ውጤቶችን ሊገዙበት የሚችሉበት ኢኮኖሚ እንዲኖራቸው ጥረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አመልክተው የጊዜ ገደብ የሌለው ድጎማ ማድረጉ ግን ኢኮኖሚውን እየገደለ እንደሚሄድ ገልጸዋል። የነዳጅ ድጎማው ሲቋረጥም ጭማሪው ለእያንዳንዱ የትራንስፖርት ተጠቃሚ ስለሚከፋፈል በኢኮኖሚው ላይ ያለው ተጽዕኖ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነም ተናግረዋል።

በመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ መምህራን ፣ ሀኪሞች እና ሌሎች ባለሙያዎች ሊቸገሩ እንደሚችሉ ጠቁመው መንግሥት ገቢያቸው የሚጨምርበትን መንገድ መፈለግ እንጂ ድጎማ እያደረጉ መዝለቁ የሚጠቅም አይደለም ብለዋል። በሌሎች አንዳንድ አፍሪካ አገራት


ፎቶ ገባቦ ገብሬ
ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ

የመንግሥት ሰራተኞች ሲቀጠሩ ደመወዛቸውን እንደግሉ ሴክተር ተነጋግረው ይቀጠራሉ ያሉት የፖሊሲ አማካሪው በእኛ አገር ይህ ተግባራዊ ቢደረግ በአገራችን አስቸጋሪ የሆነውን የአንዱን ሴክተር ደመወዝ ለማስተካከል የሁሉንም ማስተካከል እንደማያስፈልግም ጠቁመዋል።

የመንግሥት ድርጅቶች በአብዛኛው የግሉ ሴክተር ሊሰራቸው የሚችላቸውን ስራዎችን የሚሰሩ ወደ ግሉ ሴክተር እየተዛወሩ እንዲሄዱ መንግሥት ፍላጎት እያሳየ መሆኑን ጠቁመው ለዚህም ተቋማት ተቋቁመው የካፒታል ገበያ እንዲቋቋም የመጨረሻ ደረጃ እንደደረሰ ተናግረዋል። ድጎማው በሚነሳበት ጊዜ ጥንቃቄ በተሞላበት እና ሕዝቡን ሊጎዳው በማይችል መንገድ መሰራት ይኖርበታል ያሉት አማካሪው ድጎማውን መቀጠል ግን መጨረሻ ላይ አገሪቱን ለባሰ ችግር የሚዳርጋት እንደሚሆን ተናግረዋል፡

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደሚሉት የዋጋ ግሽበቱ በከፍተኛ ደረጃ እየመጣ ያለው ከገንዘብ ምንዛሪ ጋር በተያያዘ ነው። አብዛኛው መጠቀሚያ እቃዎች በተለይ የምግብ አይነቶች ስኳር ፣ዘይት፣ ስንዴ የመሳሰሉ ነገሮች ከአገር ውጭ የሚገቡ በመሆኑ የዋጋ ግሽበቱ በተለይ የምግብ ሸቀጦች ላይ በከፍተኛ ደረጃ መጨመራቸውን አስታውሰው የነዳጅ ዋጋ በሚጨምርበት ጊዜ በተወሰነ ደረጃ ለውጦች እንደሚኖሩም ጠቁመዋል።

# በክረምት ወቅት በመዲናዋ የሚከሰተውን የጎርፍ አደጋ ለመቀነስ ትኩረት ማድረጉን ኮሚሽኑ አስታወቀ

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡- ክረምት በመጣ ቁጥር በመዲናዋ የሚከሰተውን የጎርፍ አደጋ ጉዳት ለመቀነስ ትኩረት ማድረጉን የአዲስ አበባ የእሳትና የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ክረምት በመጣ ቁጥር ከሚያስቱ አደጋዎች መካከል የጎርፍ አደጋ አንዱ ነው። የጎርፉ አደጋ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በቂ ዝግጅት ተደርጓል።

በ2013 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በርካታ የጎርፍ አደጋዎች የተከሰቱ ሲሆን ከነዚህ አደጋዎች ውስጥ 25ቱ ከባድ የጎርፍ አደጋዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በአደጋው ምክንያት አስር ሰዎች ሕይወታቸው ማለፉንና አራት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብረትም መውደሙንም አስረድተዋል።

በ2014 ዓ.ም የክረምት ወቅት ተመሳሳይ አደጋዎች እንዳያጋጥሙ በልዩ ትኩረት እየተሰራ መሆኑን ተናግረው፤ ከሰባት ባለድርሻ ተቋማት ጋር በመሆን ለስራው ጠንካራ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተለይም ኮሚሽኑ ከመንገዶች ባሥልጣን፣ ከውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ ከጽዳት አስተዳደር እንዲሁም የወንዞች ተፋሰስ ባለሥልጣንን ጨምሮ ከሰባት የተለያዩ ተቋማት ጋር የጎርፍ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል የተጋላጭነት ጥናት አድርጓል። በጥናቱም 148 ቦታዎች በከተማ ደረጃ ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ መሆናቸው መለየቱን ገልጸዋል።

ጥናቱን መሰረት በማድረግ የተለዩ አካባቢዎች ላይ ለጎርፍ አደጋ እንዳይጋለጡ የመፍትሄ እርምጃ ተወስዷል። የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የተሰጠውን ድርሻ እየተገበረ ሲሆን፤ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣንና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት አደጋውን ለመቀነስ የሚያስችል የዝግጅት ስራ እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዚህም የጎርፍ አደጋ መከላከያ የድጋፍ ግንቦችን የማዘጋጀት፣ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች የማፅዳት እንዲሁም በወንዝ ዳርቻ አካባቢ የሚኖሩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ከቦታው ላይ አንስቶ ደሕንነቱ የተጠበቀ ቦታ ላይ እንዲኖሩ የማድረግ ስራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።


አቶ ንጋቱ ማሞ

የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች በበቂ ሁኔታ የሚመጣውን ጎርፍ እንዲያስተናግዱ ተደርገው ባለመሰራታቸው በርካታ የጎርፍ አደጋዎች እንዲከሰቱ መንስኤ መሆናቸውን ያነሱት አቶ ንጋቱ፤ በተጨማሪ ግለሰቦች ባዕድ ነገሮችን ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ ጉድጓድ ውስጥ በመጨመር የጎርፍ አደጋ እንዲስፋፉ ምክንያት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ችግሩን ለመፍታት የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን እንዲሁም የከተማው ጽዳት አስተዳደርና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ማህበረሰቡን በማሳተፍ በጽዳትና በዘመቻ መልክ አካባቢዎችን በማጽዳት ችግሩ እንዳይከሰት እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ችግሩን ለመፍታት በሚደረገው እንቅስቃሴ ማሕበረሰቡ የመፍትሄ አካል መሆን እንዳለበትም መልዕክት አስተላልፈዋል።

በተለይም በወንዝ ዳር አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ከቦታው እንዲነሱ በሚጠየቁበት ወቅት ፍቃደኛ በመሆን መተባበር እንዳለባቸው ተናግረዋል።

ከዚህ አልፎ ለሚደርስ አደጋ ኮሚሽኑ በከተማዋ ከሚገኙ ዘጠኝ ቅርንጫፎችና በማዕከል ደረጃ ከጎርፍ ጋር ተያይዞ ለሚፈጠሩ አደጋዎች አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሰጥ አስታውቀዋል።

ለአዲስ አበባ የእሳትና የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን እንዳስታወቀው፤ ማሕበረሰቡ አደጋ በሚደርስበት ወቅት በነፃ የስልክ መስመር 939 ወይም በመስመር ስልክ 0111555300 በመደወል ዕርዳታ መጠየቅ ይኖርበታል።

# "አሸባሪው ሕወሓት አሁንም ከጦር ጉሰማ አመሉ አልተላቀቀም''

## አቶ ደመቀ መኮንን

አዲስ አበባ፡- በመንግሥት በኩል ግጭቱ ከዚህ በላይ እንዲባባስ እና ዳግም ወደ ጦርነት እንዲገባ ምንም ፍላጎት የሌላው ቢሆንም አሸባሪው ሕወሓት አሁንም ከጦር ጉሰማ አመሉ አልተላቀቀም ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ትናንት ተቀማጪነታቸውን ብራሰልስ ላደረጉ የአውሮፓ ህብረት የፖለቲካ እና የፀጥታ ኮሚቴ አምባሳደሮች ገለፃ አድርገዋል። በአምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ ለተመራው የህብረቱ ልዑክ የተደረገው ገለፃ በሰብዓዊ ድጋፎች ፣ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ስለተከሰተው ግጭት እና መንግሥት ስላቀረባቸው የሰላማዊ አማራጭ እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈፀሙ አካላትን ተጠያቂ በማድረግና በሁሉን አካታች ብሄራዊ ምክክር ላይ ያተኮሩ ናቸው።

በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ግጭቱ ከዚህ በላይ እንዲባባስ እና ዳግም ወደ ጦርነት እንዲገባ ምንም ፍላጎት እንደሌለ ያረጋገጡት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፤ነገር ግን በሌላ ወገን አሸባሪው ሕወሓት አሁንም ከጦር ጉሰማ አመሉ እንዳልተላቀቀ እና አሁንም ዜጎችን ለጦር በመመልመል ለዳግም ወረራ እየተዘጋጀ መሆኑን ለአምባሳደሮቹ አብራርተዋል።

በሀገሪቱ የተከሰተውን ችግር በሰላም ለመቋጨትም መንግሥት ሁሉን አካታች ብሄራዊ ምክክር ለማድረግ በሂደት ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በሌላ በኩልም በትግራይ፣ አማራና አፋር እንዲሁም በሌሎች ክልሎች ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች ያልተቋረጠ



የሰብዓዊ ድጋፍ ማቅረብ የመንግሥት ቀዳሚ ትኩረት እንደነበር አቶ ደመቀ ገልፀዋል።

ያልተገደበ የሰብዓዊ ድጋፍ ለዜጎች እንዲቀርብም መንግሥት ተኩስ የማቆም ውሳኔ በማሳለፍ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች እህል እና እህል ነክ ያልሆኑ ድጋፎች ሲቀርቡ እንደነበር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

መንግሥት ከዓለምአቀፍ የሰብዓዊ ድርጅቶች ጋር በመሆን ባደረገው የተቀናጀ ጥረትም በትግራይ ክልል የሰብዓዊ ድጋፍ በተሳካ መልኩ እንዲቀርብ መደረጉንም ለህብረቱ አባላት አብራርተዋል።

የተመድ ሰብዓዊ ድጋፍ አቅራቢዎች የተመጣጠነ ምግብ ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ ነገሮች እና ክትባትን ጨምሮ የተለያዩ መድኃኒቶች በየእለቱ እንዲያጓጉዙ መደረጉን የገለፁት ሚኒስትሩ በቀጣይም ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች በአፋጣኝ እንዲቀርብ መንግሥት ፅኑ አቋም እንዳለው ተናግረዋል።

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የተፈጠረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትም መንግሥት መተማመኛ ሊፈጥሩ የሚችሉ የተለያዩ ውሳኔዎችን ማሳለፉን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቁመዋል ።

በዚህም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳ መደረጉ እና ለሰላም ሲባል ስመ-ጥር የሕወሓት አመራሮች ከእስር እንዲለቀቁ መደረጉን እንደማሳያነት ጠቅሰዋል።

የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ ተወካይ የሆኑት ኦሊሰጉን አባሳንጆ ለችግሩ መፍትሄ ለማፈላለግ ከመንግሥት እና ከሌሎች አካላት ጋር እየሰሩ መሆናቸውንና ለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት ቀናኢነቱን በተጨባጭ እያሳየ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚህ ሂደትም የአውሮፓ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ተወካይዋ አኔት ዌበር እያደረጉ ላለው የሰላም ጥረት አቶ ደመቀ ምስጋና አቅርበዋል።

የሰብዓዊ መብት ጥሰትንም በተመለከተ በዚህ ድርጊት የተሳተፉ አካላትን ተጠያቂ ለማድረግ መንግሥት ተጨባጭ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑን አስረድተዋል።

አቶ ደመቀ የአውሮፓ ህብረት ለኢትዮጵያ እያደረገ ያለውን ሁለንተናዊ ድጋፍም ያደነቁ ሲሆን የሁለቱ አካላት ግንኙነት የተሻለ በሚሆነባቸው ጉዳዮች ላይ የላቀ ትብብር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዘ ማብራሪያ የሰጡት የፍትህ ሚኒስትሩ ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ መንግሥት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ከተመድ የሰብዓዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነሮች ጽህፈት ቤት ጋር በጣምራ የተደረገውን ምርመራ እና ግኝት በሚመለከት ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን መንግሥትም የምርመራውን ውጤት እንደተቀበለው ተናግረዋል።

በትግራይ ክልል በተፈፀሙ ሰብዓዊ ወንጀለኞች ላይም ህግን የተከተለ ምርመራ መካሄዱንና ድርጊቱን የፈፀሙ አካላትን ተጠያቂ የማድረግ ሥራም እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል ።

ከትግራይ ክልል ባሻገር በአማራና አፋር ክልሎችም የተፈፀሙ ወንጀሎችን በሚመለከት ጥልቅ ምርመራ እየተካሄደ ሲሆን ወንጀሎቹ ስለመፈፀማቸው የሚያስረዱ ማስረጃዎች በአሁኑ ሰዓት በመመርመር ቡድኑ ተሰባስበው እየተተነተኑ መሆናቸውን ተናግሯል።

በዚህ ጉዳይ ላይም የአውሮፓ ህብረት በተለይ ለመርማሪ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናና ሌሎች ድጋፍ እንዲያደርግ ሚኒስትሩ አባላቶቹን ጠይቀዋል።

መቀመጫውን ብራሰልስ ያደረገው የአውሮፓ ህብረት የፖለቲካና ፀጥታ ኮሚቴ አምባሳደሮች በተደረገላቸው ገለፃ ላይ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን በአቶ ደመቀ መኮንን እና በዶክተር ጌዴዮን ጢሞቲዎስ በኩል ምላሽ ተሰጥቷቸዋል።

የአምባሳደሮች ልዑክ የኮሚቴውን ሊቀመንበር አምባሳደር ዴልፒን ፕሮንክን ጨምሮ ከ40 በላይ አባላትን ያካተተ መሆኑን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰከነ አእምሮ ለስኬት ያበቃል!

አበው የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ይላሉ። ይህ የሚያሳየን በስሜት ከመነዳት ይልቅ ነገሮችን በሰከነ መንገድ ማየትና መወሰን ይበልጥ ለስኬት እና ለድል እንደሚያበቃ ነው።

በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ በርካታ መልካም ዕድሎችና ተስፋዎች የመኖራቸውን ያህል ባለመስከንና ነገሮችን ቆም ብሎ ባለማየት የሚመነጩ በርካታ ችግሮችም አሉ። በዚህ የተነሳ በቀላሉ በመነጋገር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮች እያደጉና እየሰፉ የብዙዎችን ሕይወት እስከመቅጠፍና ሚሊዮኖችን እስከማፈናቀል ሲዘልቁ ተመልክተናል። ለዚህ ደግሞ አሸባሪው ሕወሓት የከፈተውንና ለሁለት ዓመታት የዘለቀውን ጦርነት መመልከቱ ብቻ በቂ ነው።

በዚህ ጦርነት ባለፉት ሁለት ዓመታት በርካታ ዜጎቻችን ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ ሚሊዮኖች ተፈናቅለዋል፤ ከዚህም አልፎ ለቀጣይ የልማት ዕድገታችን ይውል የነበረ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ፈሷል።

ይህ ጦርነት ከአንድ በእብሪት ከተወጠረ ቡድን የመነጨ፣ ነገር ግን መላ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያን ዋጋ ያስከፈለ ነው። አሸባሪው ሕወሓትና ጀሌዎቹ ከውልደታቸው ጀምሮ ውጤት እናገኛለን ብለው የሚያስቡት በጦርነት ብቻ በመሆኑ ከዚህ ተግባራቸው ሊማሩ የሚችሉበት አንዳችም መስከን አይታይባቸውም። ሁሉን ነገር በጠብመንጃ አፈሙዝ እንፈታለን የሚል ግብዝነት ስለተጠናወታቸው ሰላማዊ መንገድ ፈፅሞ አይታያቸውም። በዚህ የተነሳ ስለሰላም ለደቂቃም ቆም ብሎ ለማሰብ አልታደሉም።

እነዚህ ኃይሎች እየተሸነፉም ጭምር ሰላምን ለማምጣት የሚያስችል መስከን አይታይባቸውም። ለዚህ ደግሞ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከደረሰባቸው ከፍተኛ ኪሳራና በህዝባቸው ላይ ካመጡት መከራ በኋላ እንኳን መማር አቅቷቸው ዛሬም ስለጦርነት ሲሰብኩ ማየት እጅግ በጣም የሚያሳፍር ነው።

እነዚህ ኃይሎች ጉልበት እንደሌለው ፣ ነገር ግን ነገረኛ እንደሆነ አመፀኛ ልጅ እየተደበደቡም መልሰው ለግጥሚያ የሚፈራገጡ አልሞትኩም ባዮች ናቸው። ነገር ግን እንዲህ አይነት እልህ ትርፉ ለመላላጥ ካልሆነ በስተቀር አንዳችም ስኬት የሚያጎናጽፍ አይደለም።

አሁን ዓለም ጭምር ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ የምትገኝበት ወቅት ነው። በተለይ በኮቪድ ተጎድቶ የሰነበተው የዓለም ኢኮኖሚ ከዚያ በመጠኑ ፋታ ሲያገኝ በዓለማችን በአምራችነታቸው ግንባር ቀደም የሆኑት ሩስያና ዩክሬን ወደ ጦርነት መግባታቸው ለዓለም ሌላ ፈተና ይዞ መጥቷል።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ኢኮኖሚያቸው ያልጠነከረ እና ገና ከድጋፍ ያልተላቀቁ አገራት ደግሞ በዚህ ዓለምአቀፍ ችግር ይበልጥ ተጎጂ መሆናቸው አይቀርም። በመሆኑም በዚህ ወቅት ይህንን ችግር ለማለፍ ትኩረትን ሁሉ ወደሰላምና አገራዊ ኢኮኖሚን ወደመገንባት ማድረግ ይገባል።

አሁን ጦርነትና የሰላም እጦት ለአገራችን ተጨማሪ ድህነት ምንጭ ከመሆን የዘለለ አንዳችም ፋይዳ አይኖራቸውም። ሰላም ከሌለ በርካታ መሬቶች ጾማቸውን ያድራሉ። ዜጎች ተንቀሳቅሰው መስራት አይችሉም። ይህ ደግሞ የድህነት ተጋላጭነትን ይበልጥ ያሰፋል። ስለዚህ በዚህ ወቅት ትኩረትን ሁሉ ማምረት ላይ ማድረግ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ሰላም ወሳኝ ነው።

በሌላ በኩል እዚህም እዚያም ለጊዜያዊ ጥቅም ሲሉ ግጭትና አለመግባባትን ለመፍጠር በህዝብ መካከል ጥላቻን ለማንገስ የሚሰሩ ሆድአደሮች አሉ። የበሬ ወለደ ዜናን በመፈብረክ በየማህበራዊ ሚዲያ ሲነዙ የሚውሉ እና በጋዜጠኝነት ስም የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ቁጥርም ቀላል አይደለም። በተለይ በዚህ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘመን በዩትዩብ አማካኝነት ብዙ "ሼር" እና "ላይክ" ማግኘት ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ብዙዎች ከመረጃው ትክክለኝነት ይልቅ የስሜታውያንን እርካታ ማግኘትን ዋነኛ ግባቸው አድርገው ይሰራሉ። ይህ ደግሞ የነሱን ኪስ እያደለበ የአገርን ሰላም የሚያናጋ እየሆነ ይገኛል።

አሁን አሁን በዚህ በተቀደደልን የጭለማ መንገድ እንድንጓዝ በርካታ ጠላቶቻችን ከኋላ ይገፉናል። አንዳንዶቻችንንም ድግሱ ሳይገባን በዚህ የተቀደደ ቦይ ለመፍሰስ እንጥራለን። ለዚህ በተለያዩ አካባቢዎች እየተፈጠሩ ያሉ አገርን የማፍረስ ውጥኖች ማሳያዎች ናቸው። እነዚህ ኃይሎች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በንፁሃን ዜጎች ላይ ቁማር በመጫወት ለፖለቲካ ትርፍና ለኢትዮጵያ ውድቀት ሌት ተቀን ይሰራሉ። ነገር ግን እኛ ምርጫችንን ማስተካከል ይጠበቅብናል፤ የቻይናና የጃፓንን የልማት መንገድ አልያም የየመንና የሶርያን የጦርነት ጉዞ።

በመሆኑም ወደግጭት ከሚወስደን ይልቅ ወደዘላቂ ሰላምና እድገት የሚወስደንን መንገድ ቆም ብለን በመመልከት ትክክለኛውን መንገድ መከተል ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

## የትምህርት ወራትን ያሳካተተው የምገባ ፕሮግራም እና ትኩረት የሚሻው ችግሮቹ

**ምህረት ሞገስ**

ክረምት ሲመጣ ብርድ ያንሰፈስፋል፤ ባዶ ሆድ ሲሆኑ ቅዝቃዜው ይበልጥ ይበረታል። በዚህ ጊዜ የሚበላው ያለው እያሟሟቀ ትኩስ ትኩሱን ይበላል። የሌለው ደግሞ አይኑን ጨፍኖ « ዳቦ የለም እንጂ ወተት በነበረ በርሱ ማግ እያረግን እንበላ ነበረ » እያለ ከመመኘት አልፎ ትኩስ ትኩሱን የሚበላውን በማጣቱ እየተበሳጨ ይብሰከሰካል። አዋቂዎች ብቻ አይደሉም፤ ህፃናትም ሲርባቸው ስለምግብ ይመኛሉ፤ ያስባሉ፤ ባይብሰከሰኩም እየተነጫነጩ እየተጣሉ ረሃባቸው እስኪታወቅባቸው ያለቅሳሉ።

ሕፃናት በጋ ላይ በሞቀ ፀሐይ ጊዜ ያገኙት የነበረውን ምግብ ክረምት ላይ ሲያጡት ሕይወት ቀላል አትሆንላቸውም። ከብስጭት እና ከእንባቸው አልፎ ለብርድ (ለሳንባ ምች) እና ለሌሎችም በሽታዎች መጋለጣቸው አይቀርም። ይሄኔ የተወዳጁ ድምፃዊ የጥላሁን ገሠሠ ዘፈን በአዕምሮ ውስጥ መምጣቱ አይቀርም። « ዋይ ዋይ ዋይ ሲሉ፤ የረሃብን ጉንፋን ሲስሉ » እንግዲህ ክረምትና ረሃብ ተያይዘው የጉንፉን ሳል ማምጣታቸው አይቀሬ ይሆናል።

ክረምት ሲመጣ የልጆች መታመም እና መሰቃየት የተለመደ ይሆናል። እዚህ ላይ ማረጋገጫ ለማግኘት የአሁኑን ክረምት ተከትሎ በአዲስ አበባ የተለያዩ ጎዳናዎች ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ዞር ዞር በማለት ሕፃናትን ማየት ተራ ነገርን እንደመመልከት ይቆጠራል።

ክረምት እና ረሃብ ሲነሳ ወላጆቻቸውን በሞት የተነጠቁ ሕፃናት፣ ልጆቻቸውን በቀን አንድ ጊዜ እንኳን መመገብ የማይችሉ እና በቂ ገቢ የሌላቸው ወላጆች ልጆች በረሃብ እየተሰቃዩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ራሳቸውን ስተው እየወደቁ ስለመሆኑ በአዲስ አበባ መወራት ከጀመረ አሥር ዓመታት ተቆጠሩ። ከወሬው አልፎ በ2006ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮና የሴቶችና ህጻናት ቢሮ በጋራ ያደረጉት የዳሰሳ ጥናት በማስረጃ ተደግፎ እንደቀረበው ከ20ሺ በላይ የሚሆኑ ህፃናት በዛ ዓመት በቂ ምግብ ባለማግኘት የተነሳ የከፋ ደረጃ ላይ እንደደረሱ ይፋ ተደርጓል።

ተማሪዎች በረሃብ ትምህርታቸውን ለመከታተል ስለመቸገራቸው መገለፁን ተከትሎ ሕፃናትን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመመገብ መርሐ ግብር መጀመርን በሚመለከት በብዙዎች ዘንድ ሃሳቡ መጉላላት ጀምሯል። በተለይ የቀድሞ ቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ሮማን ተስፋዬ የነቃ ተሳትፎ የሚዘነጋ አይደለም።

ይህ ሃሳብ ምንም እንኳን ቀድሞ ሰብዓዊነትን ተከትሎ የተነሳ ሃሳብ ቢሆንም በተጨማሪነት ህፃናት እንክብካቤ የማግኘት መብት ስላላቸው የትምህርት ቤት ምገባ መኖር አለበት የሚል ሃሳብ መሰንዘር ቀጠለ። በአንዳንድ በጎ ፈቃደኞች በጥቂቱ ይካሔድ ከነበረ ምገባ በተጨማሪ በ220 የቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ከ22ሺህ በላይ የሚሆኑና የከፋ ድህነት ላለባቸው ተማሪዎች በእናት ወግ በጎ አድራጎት ማህበር እንዲሁም በመምህራንና በትምህርት ቤት ማህበረሰብ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት፣ ግለሰቦች እንዲሁም የተለያዩ በጎ አድራጎት ሥራ ላይ በተሰማሩ አካላት ደግሞ ከ10ሺህ 119 በላይ የሚሆኑና በቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ለሚማሩ የመንግሥት ተማሪዎች በምገባ መርሐ ግብር ተጠቃሚ መሆን ቻሉ።

ጤናማና የተማረ ማህበረሰብ መፍጠር ለአንድ አገር ህልውና መሰረት በመሆኑ ለትምህርት ቤቶች የሚውለው በጀት ለኢንቨስትመንት እና ለግንባታ ብቻ ሳይሆን፤ ለምገባም መዋል እንዳለበት ሙሉ ለሙሉ ታመነ። ተማሪዎች በቂ ምግብ ባለማግኘታቸው ምክንያት የነበረውን የተማሪ መቅረት፤ የክፍል ደረጃ መድገም እና ትምህርት ማቋረጥ ላይ የነበሩትን ከፍተኛ ችግሮች ማቃለል ተቻለ። በተጨማሪ በቂ ምግብ ሳያገኙ ተርበው ሲማሩ የሚውሉ ልጆች ትምህርቱን ለመረዳት የሚያዳግታቸው በመሆኑ በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስላለው ይመገቡ ከማለት በተጨማሪ በቂ፣ ጤናማ እና የተመጣጠነ የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብር በተገቢው መልኩ መካሔድ እንዳለበት ታምኖ በመንግሥት ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት እስከ አሁን ቀጠለ።

ይህ እጅግ በጣም ብዙዎችን ተጠቃሚ እያደረገ ያለ የምገባ መርሐ ግብር አሁን ደግሞ ከትምህርት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከሰብዓዊነት እና ልጆች በቂ ምግብ የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ በክረምትም ምግብ የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸት እንዳለበት ብዙዎች ሃሳብ በመሰንዘር ላይ ናቸው። እንደበጋው የተማሪዎች ምገባ ሁሉ የክረምት ምገባ አስፈላጊነትን ስናነሳ በእርግጥም ባዶ ምሳ ዕቃ ይዘው የሚሔዱ፤ አንዳንዴም ከጓደኞቻቸው የሚወድቅ ፍርፋሪን ለቅመው ይበሉ የነበሩ ልጆች የትምህርት መዘጋት ሆዳቸው ባዶ ሆኖ ቀናትን እንዲገፉ ያስገድዳቸዋል።

ክረምት ላይ ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ የሚያጋጥማቸውን ርሃብ መገመት አያዳግትም። ከትምህርት አንፃርም ከታየ በአንድ ወቅት ብቻ በቂ ምግብ ማግኘት ውጤታማ አያደርግም። በክረምት በረሃብ እና በበሽታ ሲሰቃዩ የነበሩ ልጆች በጋ ላይ ምግብ ስላገኙ ብቻ ጤናማ ይሆናሉ ብሎ ማመን ችግሩን ማገናዘብ አለመቻል ነው።

በትክክል ከሰብዓዊነትም ሆነ ከትምህርት ጥራት እንዲሁም ልጆች ካላቸው በቂ ምግብ የማግኘት መብት አንፃር ከታየ የበጋ ወይም የትምህርት ጊዜ ምገባ ብቻ ሳይሆን የክረምት ወቅት ምገባም ያስፈልጋል። የክረምት ምገባ ከሌለ በረሃብ ምክንያት ራሳቸውን ስተው ትምህርት ቤት ውስጥ ይወድቁ የነበሩ ልጆች ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ቤታቸውም ያለማንም ተመልካች ራሳቸውን ስተው የሚወድቁበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ነጋሪ አያሻም።

የበጋው ምገባ ከትምህርት ቤት ይቀራሉ፤ትምህርት ያቋርጣሉ፤ ክፍል ይደግማሉ በማለት እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ቢሆንም የሌሎች ተማሪዎችን ትርፍራፊ በመልቀም ይበሉ የነበሩ ሕፃናት በክረምትም ከቤታቸው ወጥተው ምግብ ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ወደ ሌላ ተግባር ማለትም ወደ ስርቆት ሊገቡ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ ሲቀጥል በጋ ላይ ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ ሊገደዱ ይችላሉ። ምክንያቱም በአንድ በኩል የስርቆት ተግባርን የሚቀጥሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። ወይም ወደ ማረሚያ ቤት የሚገቡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በሌላ በኩል ስርቆታቸው ከታወቀ የመገለልና የበታችነት ስሜት ይሰማቸዋል። ይህ ልጆቹን ቁጡና ተናዳጅ ስለሚያደርጋቸው ሌሎች ተማሪዎች ላይም ሆነ መምህራን ላይ ጫና ይፈጥራል። ይህም ተያይዞ የትምህርት ጥራት ላይ የራሱን አሉታዊ ጫና ይፈጥራል።

ይህንን ችግር ለማቃለል በተለይም በዋናነት በቀድሞ ቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ሮማን ተስፋዬ በበላይ ጠባቂነት ሴት መምህራንን የቦርድ አባል በማድረግ በ2007 ዓ.ም በተቋቋመው የእናት ወግ በጎ አድራጎት ማህበር በይፋ የተጀመረው የትምህርት ቤት ምገባ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ሲቀጥል የክረምት ጉዳይ ብዙም ትኩረት ያላገኘ በመሆኑ አሁን ግን ተገቢውን ትኩረት ማግኘት አለበት።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በ2011ዓ.ም የትምህርት ቤት ምገባ በ241 ትምህርት ቤቶች ከ311 ሺህ 523 በላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ ሆነዋል። በአዲስ አበባ የመንግሥት አንደኛ ደረጃና ቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በአጠቃላይ በሙሉ ተደራሽ የተደረገው የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብር ለ6ሺህ 969 ለሚሆኑ ሥራ አጥ እናቶች የሥራ እድል ፈጥሮላቸዋል። ይሁን እንጂ የክረምት ምገባ የለም። ይህ በተማሪዎች ፣ በወላጆች፣ በመምህራን እና ብሎም በትምህርት ጥራት ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ ከወዲሁ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ።

ዜና

# በክልሉ በሳምንት በአማካኝ ከ8 ሺ እስከ 9 ሺ ሰዎች በወባ በሽታ እየተያዙ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሶስት ወራት ውስጥ በሳምንት በአማካኝ ከስምንት ሺ እስከ ዘጠኝ ሺ ሰው በወባ በሽታ እየተጠቃ መሆኑን የክልሉ የጤና ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ጤና ቢሮ ኃላፊ አቶ እንዳሻው ሽብሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሶስት ወራት ውስጥ የወባ ወረርሽኝ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። በሳምንት በአማካኝ ከ8 ሺ እስከ 9 ሺ ሰው በወባ በሽታ እየተያዘ ይገኛል።

ባለፈው ዓመት ከሚያዝያ እስከ ግንቦት መጨረሻ 66 ሺ 14 ሰዎች በወባ መያዛቸውን ያስታወሱት አቶ እንደሻው፣ በዚህ ዓመት በተመሳሳይ ጊዜያት 106 ሺ 821 ሰዎች በወረርሽኙ ተይዘዋል። ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ38 በመቶ ጭማሪ አለው ብለዋል።

በሶስት ወር ውስጥ በአማካኝ ከስምንት ሺ እስከ ዘጠኝ ሺ ሰዎች በወባ እየተያዙ መሆኑን በየሳምንቱ የሚወጣው ሪፖርት እንደሚያሳይ አመልክተው፤ ለወረርሽኙ ምላሽ ለመስጠት ጥረት ባይደረግ ኖሮ የብዙ ሕይወት ሊያልፍ ይችል እንደነበረም አስረድተዋል።

የአየር ንብረቱ መቀየር፣ የፀጥታ ችግር፣ የአጎበር አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆንና በሕብረተሰቡ ዘንድ ወባ ቀንሷል ብሎ መዘናጋቱ በክልሉ ላለው ከፍተኛ የወባ ወረርሽኝ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም ያቆሩ ውሃዎችን የማፍሰስ ስራ አለመሰራቱ፣ መቀየር ያለበት አጎበር በሰዓቱ አለመቀየሩ፣ በጤናው ዘርፍ ላይ በታችኛው እርከን ደረጃ ያሉ ባለሙያዎች መረጃን የመተንተን ችግሮች፣ለወረርሽኝ መከላከያ የሚሆን በጀት ተይዞ አለመሰራቱ ምክንያት መሆናቸውንም አብራርተዋል።

የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው አጎበሮች እንዲቀየሩ ከጤና ሚኒስቴር ጋር መምከራቸውን የገለጹት አቶ እንደሻው፤ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ያህል አጎበር በቅርቡ በ36 ወረዳዎች ይሰራጫል ብለዋል። ይህም ወረርሽኙን ለመግታት በሚደረገው ሂደት ውጤታማ ስራ ለመስራት ያግዛል።

አዲስ ጸረ ወባ ኬሚካል ወደ ክልሉ መግባቱን ጠቁመው፤ በ46 ወረዳዎችም ርጭቱ እንደሚከናወን ተናግረዋል።

እንደ ጤና ቢሮው ኃላፊ ገለጻ፤ በክልሉ የወባ ወረርሽኝ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ምላሽ ለመስጠት ከክልል ጀምሮ ከአመራሩ ጋር ውይይት ተደርጎ ወደ ስራ ተገብቷል። በወባ ወረርሽኝ ላይ የሚሰሩ የክልሉ የጤና ቡድኖች ወረርሽኙ በተከሰተባቸው አካባቢዎች በመንቀሳቀስ እየሰሩ ነው።

ወረርሽኙ በስፋት የሚታይባቸው ደቡብ ኦሞ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ከንባታ ጠንባሮ፣ ጎፋ ዞን ሲሆኑ በልዩ ወረዳ ደራሼና ባስኬቶ ተጠቃሽ ናቸው። ነገር ግን በሁሉም አካባቢዎች ወባ አለ። ወረርሽኙን ለመከላከል ለ36 ወረዳዎች የአጎበር ስርጭትና በ46 ወረዳዎች የኬሚካል ርጭት ስለሚደረግም ስርጭቱ በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀንስበት ሁኔታ እንደሚፈጠር የጤና ቢሮው ኃላፊ ተናግረዋል።

ህዝቡ ከመሰል ወረርሽኞች ራሱን ለመከላከል ቅድመ ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ የክልሉ ጤና ቢሮ አሳስቧል።

# በ5 ነጥብ 8 ቢሊዮን...

የሚቻለው ጠንክሮና ተግቶ በመስራት ነው። ይህንንም ማድረግ እንደሚቻል አቶ ክብሩይስፋ አሳይተዋል።

አንድ ሰው ተግቶና ጠንክሮ መስራት ከቻለ የማይለወጥ ነገር የለም ያሉት አቶ ሽመልስ፤ አገር የሚያሻግሩትና የሚያጸኑት ወሬኞች ሳይሆኑ እንደ አቶ ክብሩይስፋ አይነት የተግባር ሰዎች ናቸው ብለዋል።

የብረት ኢንዱስትሪ በአገራችን ካሉ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ወሳኝና በትልቁ እየተፈተንበት ያለ ሴክተር ነው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ማሸጋገር የሚቻለው ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ መሰረታዊ ለውጥ ከመጣ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል።

ከተሞች፣ ገጠሩ መዘመንና መገንባት አለበት ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ግድቦች፣ መንገዶች፣ ኢንዱስትሪዎች መገንባት አለባቸው። ለዚህ ስኬት ብረት ዋና እና ወሳኝ ምሰሶ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አገራችን በቢሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘብ እያወጣች የምትገዛውን ብረት በአገር ውስጥ በመተካት እሴት በመጨመር ለገበያ ለማቅረብ እንደ ታዳሽ አይነት ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊ ናቸው። አቶ ክብሩይስፋ ታዳሽን ገንብተው አገርን ስላኮሩ እናመሰግናለን ብለዋል አቶ ሽመልስ።

የታዳሽ ብረታብረት ኢንዱስትሪ ባለቤት አቶ ክብሩይስፋ ተክሉ ፤ መርካቶ በ27 ብር ደመወዝ የተጀመረው የግል የሥራ ጥረት በአገሪቱ ካሉት ታላላቅ ተቋማትና ፋብሪካዎች እስከ 90 በመቶ የሚደርሰውን ምርቶቻቸውን በመግዛት በመርከብ በማስጫን ለደቡብ ኮሪያው ኪንግሃምና ሌሎች የቻይና ኩባንያ ወኪል በመሆን ይሸጡ እንደነበር ተናግረዋል። ዛሬ ግዙፍ ፋብሪካ መገንባት መቻል ትልቅ ስኬት መሆኑንም ገልጸዋል።

በ50 ሺ ካሬ ሜትር መሬት ላይ የተገነባው ታዳሽ የብረት ኢንዱስትሪ 5 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል። ኢንዱስትሪው አካባቢን የሚበክል ምንም አይነት አየርም ሆነ ፍሳሽ እንዳይኖር ዓለም አቀፍ ደረጃን የISO መመዘኛ መስፈርትን አሟልቶ የተገነባ ነው ሲሉም ባለሃብቱ አብራርተዋል።

እንደ ባለሃብቱ ገለጻ፤ ኢንዱስትሪው ሙሉ ለሙሉ ግንባታው ተጠናቆ ምርት ማምረት ጀምሯል፤ በቀን 450 ቶን ብረት የማቅለጥ አቅም አለው። ፋብሪካው 600 ቶን ፌሮ በቀን ያመርታል። የፋብሪካው መገንባት በዘርፉ ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይቀንሳል። ከ700 በላይ ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ፈጥሯል ።

የታዳሽ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ባለቤት በፌዴራልና በኦሮሚያ ክልል ደረጃ ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል የ15 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አድርጓል። ለፋብሪካው እውን መሆን አስተዋጽኦ ላደረጉ የመንግሥት ተቋማትና ለፋብሪካው ሰራተኞች እውቅና ተሰጥቷል።

የፋብሪካው ባለቤት ለኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች የሚሆን አምስት ሚሊዮን ብርና በፌዴራል ደረጃ ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል 10 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደርገዋል።ባለሃብቱ በዱከም ከተማ ከ10 ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ አንድ ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር አስፋልት መንገድ የገነቡ ሲሆን በሱማሌ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር፣ ለኮሮና ወረርሽኝ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ ለ700 አባወራዎች ድጋፍ ማድረጋቸውን አስታውቀዋል።

# የሁሉንም ርብርብ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደ ጽሕፈት ቤቱ መረጃ፤ በክልሉ ከ1 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ የእለት ደራሽ እርዳታ ጠባቂ ሆኗል። በወረራው አማካኝነት ከስድስት መቶ አርባ አምስት ሺህ በላይ ሕዝብ የተፈናቀለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሦስት መቶ ሺህ ስምንት ሰዎች ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል።

በአሁኑ ሰዓት ሦስት መቶ 36 ሺህ ተፈናቃዮች በክልሉ በሚገኙ 17 ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ እንደሚገኙ የተገለጸ ሲሆን፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት ድጋፍ እየደተረገላቸው ይገኛል ተብሏል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድኑ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ መጠለያ ጣቢያዎችን የጎበኘ ሲሆን አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ ተፈናቃዮችን አነጋግሯል።

አብዛኛው የበራህሌ ወረዳ ተፈናቃይ በአካባቢው ጥሩ ኑሮ ይኖር ነበር የሚሉት በጉያህ መጠለያ ጣቢያ የተጠለሉት የበራህሌ ወረዳ ነዋሪው ሼኽ መሐመድ፤ አሁን ሁሉም በሚባል ደረጃ የወረዳው ሕዝብ የእለት ደራሽ እርዳታ ጠባቂ እንደሆነም ያስረዳሉ።

ሼኽ መሐመድ ለተፈናቃዮች የሚሰጠውን እርዳታ በተመለከተ ሲያብራሩ፤ ወደ መጠለያ ጣቢያው ከገቡ አምስት ወራት እንደተቆጠሩ ተናግረው፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ ድጋፎች እየተደረገላቸው መሆኑንም ገልጸዋል። አክለውም፣ ድጋፉ አሕዝቡ ፍላጎት አንጻር በቂ አይደለም ብለዋል።

በተጨማሪም፣ እርዳታው የሚሰጠው ለአባወራ መሆኑንና የቤተሰብ ቁጥር ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑን ጠቅሰው፤ አነስተኛ የቤተሰብ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ተጠቃሚዎች ሲሆኑ ብዛት ያላቸው የቤተሰብ አባላት የሚያስተዳድሩ አባወራዎች ግን ተጎጂዎች እንደሆኑም ጠቁመዋል።

ቤተሰብን በእርዳታ ምግብ ማስተዳደርና ኑሮን በመጠለያ ጣቢያ መግፋት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን የገለጹት ሼኽ መሐመድ፤ የአካባቢያቸው ሰላም ከተመለሰና ሁኔታዎች ከተመቻቹ ተፈናቃዮች ለዓመታት ወደኖሩበት አካባቢ ለመመለስ እንደጓጉ አስረድተዋል።

በመጠለያ ካምፑ ውስጥ ላሉ ተፈናቃዮች በመንግሥትና በሌሎችም የረድዔት ድርጅቶች ፉርኖ ዱቄት፣ ዘይት፣ ስንዴ፣ አተርና ሌሎችም ምግብ-ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ እንደሚያገኙ የተናገሩት ደግሞ የአብአላ ወረዳ ተፈናቃይ ወይዘሮ ዘምዘም ናጂ ናቸው።

ወይዘሮ ዘምዘም እንደሚገልጹት፤ ከስምንት ልጆቻቸውና ከብዙ የልጅ ልጆቻቸው መጠለያ ካምፕ ከመጡ አምስት ወራት ሆኗቸዋል። ሁሉም ልጆቻቸው አብአላ በነበሩበት ጊዜ ሠርተው ይበሉ የነበረ ሲሆን አሁን ግን የእለት ደራሽ እርዳታ ጠባቂ ሆነዋል ብለዋል።

ወይዘሮ ዘምዘም በመጠለያ ጣቢያው ያለውን ችግር በተመለከተ ሲናገሩ፤ በእርዳታ የሚሰጠው ስንዴ ጥሬ በመሆኑና ወፍጮና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ባለመቅረባቸው ምክንያት ተረጂዎች በእርዳታ ያገኙትን ስንዴ ለመሸጥና የተዘጋጀ ምግብ ለመግዛት ይገደዳሉ፤ በዚህ ምክንያት ለአንድ ቤተሰብ ለአንድ ወር ተብሎ የሚሰጠው እርዳታ በጥቂት ቀናት ውስጥ ያልቃል ብለዋል።

የበራህሌ ወረዳ ተፈናቃዮች እርዳታ አስተባባሪ አቶ መሐመድ ሙሳ በበኩላቸው፤ ከመንግሥት በተጨማሪ በዓለም የምግብ ፕሮግራም፣ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እና በሌሎችም ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች አማካኝነት ለተፈናቃዮች ስንዴ፣ ሩዝ፣ ፉርኖ ዱቄት፣ ዘይት፣ አተር፣ የምግብ ማብሰያና ሌሎችም እርዳታዎች እየቀረቡ መሆኑን ገልጸው፤ ባለፉት ሁለት ወራት የእርዳታ አቅርቦቱ እየተቀዛቀዘ መሆኑን አስረድተዋል።

የተፈናቃዮች የምግብ ፍላጎት ለማሟላትና በዘላቂነት ለማቋቋም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊረባረቡ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የአፋር ክልል የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዋና ኃላፊ አቶ መሐመድ ሑሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሕወሓት የሽብር ቡድን ወረራ፣ በድርቅ፣ በጎርፍ አደጋ፣ በአንበጣ መንጋና በሌሎችም ምክንያቶች በክልሉ የምግብ ዋስትናቸው ጥያቄ ውስጥ የገባ ዜጎች ቁጥር አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ደርሷል።

እንደ አቶ መሐመድ ገለጻ፤ በሽብር ቡድኑ ወረራ ምክንያት ከተፈናቀሉ ስድስት መቶ 45 ሺህ ዜጎች ሦስት ስምንት ሺህ ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል፤ በአሁኑ ሰዓት ሦስት መቶ 36 ሺህ ተፈናቃዮች በክልሉ ባሉ 17 ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ይገኛሉ።

ተፈናቃዮችን ወደነበሩበት አካባቢ ለመመለስና በዘላቂነት ለማቋቋም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ዘርፈ-ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውም አብራርተዋል።

የሽብር ቡድኑ ወረራ በፈጸመባቸው አካባቢዎች የነበሩ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሙሉ በሙሉ በመዘረፋቸውና በመውደማቸው ተቋማቱ ድጋፍ ተደርጎላቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በቅንጅት እየሠራ ነው ያሉ ሲሆን፤ ተፈናቃዮቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመመለስ ሌሎችም ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ በጀት በመመደብ በምግብ፣ በውሃ፣ በሕክምና፣ በመጠለያና ሌሎችም ቁሳቁሶች አቅርቦት አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ አድርጓል ያሉት ዋና ኃላፊው፤ “ችግሩ ከአቅማችን በላይ ሲሆንብን ለብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ጥሪ አቅርበን የፌዴራል መንግሥትም የሚችለውን ሁሉ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል” ሲሉ ገልጸዋል።

ክልሉ ያለበትን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች በተመለከተ ከሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ጋር ባለው የጋራ ፎረም አማካኝነት በተቀናጀ ጥናት ላይ ተመስርቶ ለተቋማቱ ጥያቄ ማቅረቡን የገለጹት አቶ መሐመድ፤ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመናበብ ዓለም አቀፍ ተቋማት ለአፋር ሕዝብ አጋርነታቸውን እንዲያሳዩ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል፤ በዚህም መሰረት ዓለም አቀፍ ተቋማት ጥሩ ምላሽ እንደሰጡም አቶ መሐመድ አክለው ገልጸዋል።

# “ሽብርተኝነትን በመዋጋት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የጋራ ቤታችን የሆነችውን ኢትዮጵያን እንጠብቃለን” በሚል መሪ ሃሳብ ሽብርተኝነትን ለመመከት የተዘጋጀ ሀገር አቀፍ የፀጥታና ደህንነት ተቋማት የሁለት ቀናት ሲምፖዚየም ማጠቃለያ ላይ እንደገለጹት ፤ ሽብርተኝነትን አጥብቀን በመዋጋት መንግሥትንና ሕዝብን ትኩረታቸውን ሙሉ በሙሉ ወደ ሰላምና ወደ ልማት እንዲመልሱ የሚያስችል ሁኔታ እንፈጥራለን።ለዚህም ሁሌም በትጋት እንሰራለን።

በውይይቱ ላይ ጠቃሚ ሃሳቦች መነሳታቸውን ያነሱት ዳይሬክተሩ በሲምፖዚየሙ በተነሱ ውይይቶች ሽብርተኛነትን በመከላከል ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ሀገራዊ የፀጥታ ሥራችንን ገምግመናል ብለዋል።

ሽብርተኝነት የመንግሥትም የሕዝብም ስጋት ስለሆነ በዚህ ዙሪያ ጠንካራ ሥራዎች ይሠራሉ ሲሉም ተናግረዋል።

በሀገሪቱ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከሶማሊያና ከየመን መሠረታቸውን ያደረጉ የሽብርተኝነትና የአክራሪነት እሳቤዎች እንዳሉ በውይይታችን አንስተናል ያሉት አቶ ተመስገን፤ ከውጭና ከውስጥ በሚደረጉ ፍልሰቶች አሸባሪዎች ሕዋስ እንዳይገነቡ ከፍተኛ ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል።

አቶ ተመስገን የሽብርተኞች ባህርይ መቀየሩንም አንስተዋል። በአመራርና በአባላት ስብጥር የሽብርተኞች ባህሪና አዝማሚያ ያለበት ደረጃ እንደተገመገመ ጠቁመው፤ ከዚህ በፊት አንድ ሃይማኖት እና አንድ ብሔር ላይ ይታዩ የነበሩ የሽብርተኝነት እና የአክራሪነት አዝማሚያዎች መለወጣቸውን አብራርተዋል።

በዚህም ሽብርተኞች የተለያዩ ሃይማኖቶችንና ብሔሮችን በማቀናጀት እኩይ ዓላማቸውን ለማሳካት እየጣሩ መሆኑን ተናግረዋል።

የቀጠናው ሀገራት የውስጥ ክፍተት ሽርተኝነትን ለመሸከም ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል ያሉት አቶ ተመስገን፤ ሽብርተኞች የቀጣናውን አለመረጋጋትንና ምርጫን በመጠቀም በግልፅም በስውርም ወደ መንግሥት መዋቅር ለመግባት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው ብለዋል።

ሽብርተኝነትን መከላከል የጋራ ሥራ መሆኑን ከበፊቱ ጊዜ በበለጠ መግባባት ላይ ደርሰናል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ሽብርተኝነትን አጥብቆ ለመዋጋት የሚያስችሉ ውሳኔዎች በጉባዔው መተላለፋቸውን ገልፀዋል።

ፀረ ሽብር ግብረ ኃይሉን በጥብቅ መምራት እና መድረኮችን ፈጥሮ መረጃዎችንና ልምዶችን መቀያየር እንዲሁም ዋናው የሽብር የተጋላጭነት ምንጩ የውስጥ ክፍተት በመሆኑ የሕግ ማስከበር ሁኔታን አጠናክረን ማስቀጠል ላይ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ስደተኞች በሚገባ ማጥራት ላይ ጠንካራ ሥራዎች እንደሚሠሩም ተናግረዋል።

ሽብርተኝነትን በመከላከል ላይ ጠንክሮ በመሥራት ሕዝባችንን ከሽብርተኝነት አደጋ እንታደጋለን ያሉት አቶ ተመስገን፤ በሽብርተኝነት ላይ ያለንን ጠንካራ አቋም በተግባር በማስደገፍ የማትደፈር፤ በኢኮኖሚም የበለፀገች ሀገር ለመፍጠር ያለንን ህልም ማሳካት እንችላለን ሲሉ ገልፀዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ለሀገር የመታመን ጥግ...!

በሀገራችን እንደ ወረርሽኝ በስፋትና በፍጥነት እየተዛመተ ስለመጣውና ከግለሰብም፣ ከተቋምና ከመንግስትም ጋር ያለንን ግንኙነት በብርቱ እየፈተነ፤ ወዲህ ደግሞ የዕለት ተዕለት የህይወታችን አካል ስለሆነውና መጠራጠርን እየጎነቆለ ስላለው "የማመን ኪሳራ"ወይም"ትረስት ዴፊሲቲ" አልያም "ትረስት ዲስፐሌስመንት" በቀጣይ ለማጠናቀር ላሰብሁት መጣጥፍ መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ በወቅቱ አለምን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ አነጋግሮ ስለነበር ፤ አለምአቀፍ ሚዲያው ዳር እስከ ዳር ተቀባብሎ ስለዘገበው ፤ በርካታ ዘጋቢ ፊልሞች ፣ ፊልሞች ስለተሰሩለትና አያሌ መጽሐፍት ስለተጻፉለት አንድ ሞልቶ ስለፈሰሰ መታመንና ጽናት እነሆ ብያለሁ። እገረ መንገዳችሁንም ራሳችሁን በባለታሪኩ ስፍራ አስቀምጣችሁ ትገመግማላችሁ። የመታመን ኪሳራችሁንም ትተሳሰባላችሁ ።

መቶ አለቃ ኦኖዳ በ2010 ዓም ከአውስትራሊያው ABC ቴሌቪዥን ጋር በነበረው ቃለ መጠይቅ ፤ " ቆፍጣና መኮንን ነኝ። የተሰጠኝን ግዳጅ እወጣለሁ ። ይሄን አለማድረግ ለእኔ የሞት ሞትና ትልቅ ውርደት ነው ። "ነበር ያለው፤ ኦኖዳ በኋላ ላይ ደግሞ ፤" እጅ አልሰጥም ፡- የ30 አመታት ጦርነቴ ፤ " በሚል ለንባብ ባበቃው ግለ ማስታወሻ ፤" የአዛዤ የመጨረሻ ትዕዛዝ በጽናት ተዋጋ ! "የሚል ነበር ። እጅ ስጥ የሚለው ትዕዛዝ ከንጉሱ ወይም ከበላይ አዛዦቼ እስኪደርሰኝ ድረስ ለ30 አመት በጽናት ትጥቄን ከወገቤ ሳልፈታ በጽናት ቆይቻለሁ ። በማለት ለሀገሩና ለንጉሱ ያለውን ፍጹም ታማኝነት ያለምንም ማወላዳት ገልጿል ።

ኦኖዳ በሰው ሀገር ጫካ ብቻውን ቀረ ። ጓዶቹን አንድ በአንድ አጣ። ራሱን እንዳያጠፉ የቅርብ አዛዡ ወታደራዊ ትዕዛዝ ትላንት ያዳመጠው ያህል በእዝነ ህሊናው ህያው ሆኖ ይሰመዋል። በስሩ የሚያዝዘው ወታደር እንደሌለው ሲያስብ የሀገሩንና የንጉሱን አደራ የበላ እየመሰለው በጥፋተኝነት አባዜ ከራሱ ጋር ይወዛገባል ። መቶ አለቃ ከ30 አመታት በፊት እጅ መስጠትም ሆነ ራስን ማጥፋት በጥብቅ የተከለከለ ነው ብሎ ወታደራዊ ትዕዛዝ የሰጠው ሻለቃ መልሶ እጅ ስጥ ሲለው መጀመሪያ ክው ብሎ ደነገጠ ከዚያ የሚሰማውን ለማመን ተቸገረ ።

ግራ ተጋባ። ለተወሰኑ ደቂቃዎች ወደ ቀልቡ ለመመለስም ተቸገረ ።

በ1941 ዓም ጃፓን ፤ ሆኖሉሉ ፣ ሀዋይ የሚገኘውን "ፐርል ሀርበር" የተሰኘውን የአሜሪካ የባሕር ኃይል ማዘዣን ድንገት በአየር አጥቅታ ከ2400 በላይ ወታደሮችን መግደሏ ፤ በርካቶችን ቁስለኛ ማድረጓና ተዋጊ መርከቦችንና አውሮፕላኖቹን መደምሰሷ አሜሪካን የ2ኛውን የአለም ጦርነት እንድትቀላቀል ምክንያት ሆኗታል። ለመጀመሪያ ጊዜ የአቶሚክ ቦንብ ለመጠቀሟ እንደ አንድ መግፍኤ ተደርጎም ይወሳል ፡፡ (በነገራችን ላይ ሁሉም የዘመን አቆጣጠሮች እንደ አውሮፓውያን ናቸው ) በዚህም የነጋሳኪና የሒሮሽማ ከተሞች ወደ ፍርስራሽነት ተቀይረዋል ፡፡ ከሁለቱ ከተሞች ወደ 230ሽ የሚጠጉ ነዋሪዎች ሲገደሉ የተረፉት ደግሞ የዘር ሀረጋቸው በአቶሚክ ቦምቡ ጠንቅ ዛሬ ድረስ ጤናቸው እየታወከ መሆኑ ይነገራል፡፡ ለዚህ ነው በአንዳንድ ኃይሎች ዘንድ የአቶሚክ ቦንብ የ2ኛውን የአለም ጦርነት በማስቆም ረገድ አስተዋፆ እንዳለው የሚታመነው ። የወቅቱ የጃፓን ንጉስ ሒሮሂቶ በሀገሩ ነገስታት ታሪክ እንኳን ሊፈጸም በፍጹም ሊታሰብ የማይችል ውሳኔ አሳለፈ ። በሬዲዮ ቀርቦ በአቶሚክ ቦንብ ሒሮሽማና ነጋሳኪ መውደማቸውን፤ ጆሴፍ ስታሊን በጃፓን ላይ ጦርነት ማወጁን ፤ ጦሩም ወደ ማንቹሪያ እየገሰገሰ ስለሆነ በሳምንታት ውስጥ ሰሜናዊ ደሴቷን ሆካይዶ ሊቆጣጠር ስለሚችል ያለን ብቸኛ አማራጭ ለባለቃልኪዳኑ ሀገራት እጃችንን መስጠት ነው በማለት የጃፓንን መራር ሽንፈት ለሕዝቡ አረዳ ።

ለ 30 አመታት የጫካ ሙዝ ፣ የዘንባባ ገውዝና የሩዝ ቃርሚያ በመብላት ህይወታቸውን አቆይተዋል ። በሽፍትነት ዘመናቸው ከፊሊፒንስ ወታደሮችና ከደሴቲ ነዋሪዎች ጋር በተደጋጋሚ ተታኩሰዋል

ጃፓን በ2ኛው የአለም ጦርነት በአሜሪካ ከተሸነፈች በኋላ ፤ በ1945 ሙሉ በሙሉ እጇን ለመስጠት ተገዳለች፤ ጥቂት የማይባሉ የጦር ጄኔራሎቿ፣ መኮንኖችና ወታደሮቿም ይህን መሪር ሀቅ ላለመቀበል እጅ ላለመስጠት ለቀናት ፣ ለሳምንታት አንገራግረው ነበር ፡፡ ሂሮ ኦኖዳ የተባለው መኮንን ግን እስከ 1974 ዓም ድረስ ለ30 አመታት የሀገሩን መሸነፍና እጅ መስጠት አምኖ መቀበል አልፈለገም ፡፡ እናም በባዕድ ሀገር ጫካና ተራራ ፋኖ ሆነ ። " ሶስት ወይም አምስት አመት ሊወስድብን ይችላል ። ምንም ይሁን ምን ተመልሰን እንደርስልሀለን፤ " ሻለቃ ዮሺሚ ታኒጉኪ ለዛን ጊዜው ወጣት የመቶ አለቃ ሒሮ ኦኖዳ በወርሀ የካቲት መጨረሻ 1945 ዓ.ም ላይ ቃል ገብቶለት ነበር ። ሆኖም ሻለቃው የገባውን ቃል ኪዳን የፈጸመው በቃሉ መሠረት በሶስትና በአምስት አመታት ሳይሆን ከ30 አመታት በኋላ ነው። የለበሰው ወታደራዊ ፋቲግ ወይም የደንብ ልብስ በላዩ ላይ አልቆ ተርዞና ተጎሳቅሎና ገርጅፎ እስከ 1974 ዓ.ም ለ30 አመታት መሽጎ ከነበረበት የፊሊፒንስ ጫካ ፍጹም ተለውጦ ወደ ጠበቀው አዲስ አለም ወጣ ።

በነገራችን ላይ በ1959 ዓ.ም የጃፓን መንግስት የመቶ አለቃ ኦኖዳን ሞት በይፋ ለቤተሰቦቹ አረድቶ ነበር። ይሁንና ኖሪዎ ሱዙኪ የተባለ ገድለኛ ጃፓናዊ ወጣት ከልጅነቱ ጀምሮ ስለ መቶ አለቃ ኦኖዳ ጽናትና ጀብድ እየሰማ ስላደገ፤ በፊሊፒንስ ደሴት በህይወት ሳይኖር እንደማይቀር ሲዘገብ ሲሰማ ይሄን ተአምረኛ ሰውማ አፈላልጌ ማግኘትና ወደ ሀገሩ ማምጣት አለብኝ ብሎ ቃል ገብቶ ፤ አፈላልጎ በማግኘትም ታሪክ ለመስራት ጓዙን ቀርቅቦ ተነሳ። እንደፎከረውም በ1974 ዓ.ም አፈላልጎ ከተደበቀበት የፊሊፒን ጫካ አገኘው ። ኦኖዳ ከሱዙኪ ፊት ለፊት እንደተገጣጠመ አቀባብሎ ግንባሩን ሊፈረክሰው ነበር። ሆኖም ሱዙኪ ኦኖዳን ቢያገኘው ምን ማለት እንዳለበት ቀድሞ ተዘጋጅቶና አጥንቶ ስለነበር ሲገናኙ ፈጥኖ እጁን ወደ ላይ በማንሳት ፤" ኦኖዳ _ሳን የጃፓን ንጉስና ሕዝብ ስለ ደህንነትህ እያሰቡና እየተጨነቁ ነው ፤ "ሲለው ፤ ደግኖበት የነበረውን ጠመንጃ አፈ ሙዝ ዘቀዘቀው ። በማስከተልም ጦርነቱ ከተጠናቀቀ 30 አመት እንደሆነና እሱም ትጥቁን ፈቶና እጁን ሰጥቶ ወደ ሀገሩ መመለስ እንዳለበት ነገረው። ሆኖም የኦኖዳ ለሀገሩ የመታመን ጥግ ከአጽናፍ አጽናፍ የተሻገር ፤ ከአለት የጸና ነውና ፤ ይፋዊ ትዕዛዝ ከሀገሬ ካልደረሰኝ እጅ አልሰጥም ብሎ አሻፈረኝ አለው።

ሱዙኪም ወደ ሀገሩ ተመልሶ ኦኖዳን እንዳገኘው ገልጾ አብሮት የተነሳውን ፎቶም በማስረጃነት አቀረበ። ለሀገሩና ለንጉሱ ምን ያህል ታማኝ እንደሆነ ለሀገሩ ልጆችና ለመላው አለም አሳየ ። በመላ ጃፓንም በአለምም መነጋገሪያም ሆነ። ገድለኛው ሱዙኪ ከወራት በኋላ ከጃፓን መንግስት እጅ እንዲሰጥ የሚያዝዝ መልዕክት የያዘ ልዑክ ጋር ወደ ፊሊፒንስ ተመለሰ ። የመቶ አለቃ ኦኖዳ ታላቅ ወንድምና ከ30 አመታት በፊት እንደርስልሀለን ብሎት የነበረው የቀድሞ አዛዡ ሻለቃ ታኒጉኪ የልዑኩ አባል ነበሩ ። የዚህን ጊዜ አመነ ። ትጥቁን ፈታ ። አሪሳካ 99 ጠብመንጃውን ከእነ 500 ጥይቱ ፣ ሳንጃውንና ቦንቡን አስረክቦ እጁንም ሰጠ ። ወደ መዲናዋ ማኒላ ተወስዶ በወቅቱ የፊሊፒንስ ፕሬዚዳንት ፈርዲናንድ ማርቆስ ፊት ቀርቦ ሳሙሪ ጉራዴውን ዝቅ አደረገ ። ፕሬዝዳንቱም በምላሹ ምህረት አደረጉለት። ከ2ኛው የአለም ጦርነት እጁን የሰጠ የመጨረሻ የጃፓን መኮንን ሆነ።

መጋቢት 19 ቀን 1922 ዓ.ም ካይናን ውስጥ ዋካያማ ጃፓን ተወለደ ። ሃያ አመት እንደሞላው ኦኖዳ የጃፓንን ጦር ተቀላቀለ ። ከዚያ ተመርጦ በናካኖ የወታደራዊ ደህንነት ትምህርት ቤት ስልጠናውን ተከታተለ። በቆይታው የሽምቅ ውጊያ ፣ ፍልስፍና ፣ ታሪክ፣ ማርሻል አርትና ድብቅ ዘመቻን ተማረ ። ይህ የተሟላ ስልጠና ነው በጽናት ፈተናዎችን እንዲያልፋቸው ያስቻለው። ብሂሉስ ላብ ደምን ያድናል እማይደል ። እሱና ሶስት ባልንጀሮቹ በፊሊፒንስ ሉባንግ ከአካባቢው ሰዎችና ከአሜሪካ ተላላኪዎች ጋር በተደጋጋሚ የሽምቅ ውጊያ አድርገዋል። በጦርነቱ የመጨረሻዎቹ ወራት አካባቢ አሜሪካ ከወግ አጥባቂ የጃፓን ወታደሮች ጋር ፊት ለፊት እስከመፋጠጥ ደርሰው ነበር ።

ሆኖም በመስከረም 1945 ዓ.ም ጃፓን በቃል ኪዳኑ ሀገራት ተሸንፋ እጇን ብትሰጥም እነ ኦኖዳ ግን ይሄን ማመንና እጅ መስጠት አልፈለጉም ። መቶ አለቃ ኦኖዳ ከፍ ብዬ ለጠቀስሁት የአውስትራሊያ ቴሌቪዥን ፤ "ጦርነቱ እንደአበቃና ጃፓንም ተሸንፋ እጇን እንደሰጠች የሚገልጹ በራሪ ወረቀቶች ከአየር እየተጣሉ ቢደርሱኝም ጹሑፎቹ የመረጃ ግድፈት ስለነበረባቸው አምኜ አልተቀበልኋቸውም። ይልቁን በአሜሪካ የተቀነባበረ ደባ ሊሆን ይችላል በሚል አላመንኋቸውም " ብሏል።

ለ 30 አመታት የጫካ ሙዝ ፣ የዘንባባ ገውዝና የሩዝ ቃርሚያ በመብላት ህይወታቸውን አቆይተዋል። በሽፍትነት ዘመናቸው ከፊሊፒንስ ወታደሮችና ከደሴቷ ነዋሪዎች ጋር በተደጋጋሚ ተታኩሰዋል። በዚህም 30 ሰዎችን ገድለዋል። ሆኖም መቶ አለቃ ኦኖዳ በ1974 ዓ.ም ብቸኛ ተቅበዝባዥ ሽፍታ ነበር ። ከባልጀራዎቹ አንዱ በ1950 ዓ.ም ለፊሊፒንስ ጦር እጁን ሰጠ ። ሁለቱ በ1954 እና በ1972 ዓ.ም ከደሴቷ ፓሊሶች ጋር በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ሞተዋል ። የወቅቱ የፊሊፒንስ ፕሬዚዳንት ፈርዲናንድ ማርከስ በሽፍትነቱ ዘመን ለፈጸማቸው ወንጀሎች ምህረት አድርገውለት ወደ ሀገረ ጃፓን ተመለሰ። የ52 አመቱ ጎልማሳ መቶ አለቃ የጀግና አቀባበል ተደረገለት። አለም ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ገድሉን ተቀባበለው። ሆኖም ጃፓን እጅግ ተለውጣ ዜጎቿም ብልጭልጭ ቁሳቁስ አምላኪዎች ሆነው ስላገኛቸው ራሱን ከዚህ ጋር ማላመድ ቸገረው ። በቀጣዩ አመት ግርግርና ትርምስ ከበዛበት የጃፓን የከተማ ህይወት በመሸሽ የሀገሩ ቅኝ ግዛት ወደነበረችው የብራዚሏ ሳው ፓውሎ በመሔድ ከብት አርቢ በመሆን ጸጥ ያለና የተረጋጋ ህይወት በመኖር የህሊና እረፍት አደረገ ። ወዲያው የጃፓን ሻይ አፈላል ስነ ስርዓት አስተማሪ የነበረችውን ማቼ ኦኑኩን ውሃ አጣጭው አደረገ ። አገባ።

በ1984 አንድ ወጣት ከፈተና በመውደቁ ተበሳጭቶ ወላጆቹን መግደሉን ጋዜጣ ላይ ሲያነብ ፤ ወጣቱ ፈተናዎችን የማለፍ የህይወት ክህሎት ቢኖረው ኖሮ ለውድቀቱ ቤተሰቦቹን ተጠያቂ አያደርግም ነበር በሚል እልህና ቁጭት ፤ እንደኔ በፈተና የማይበገር ትውልድ መቅረጽ አለብኝ በሚል ኦኖዳ በዚሁ አመት ወደ ጃፓን በመመለስ ወጣቶች ችግርንና ፈተናን እንዴት ተቋቁመው ማለፍ እንደሚችሉ የሚያስተምር የ"ኦኖዳ የወጣት ካምፕ"ን አቋቋመ ። እንደ ዮሬው ሳሙራይስ መቶ አለቃ ኦኖዳ ከጥንቱ የጃፓን ወግ ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ነበር ። የጃፓንን ባህላዊ እሴቶችና የመስዋዕትነትን ዋጋ በተግባር ኖሮ ያሳየ ጀግና ነበር ። በ1974 ዓ.ም ለመቶ አለቃ ፤" 30 አመታት ሙሉ ጫካ ስትኖር ምን ነበር የምታስበው ? " ተብሎ ሲጠየቅ ፤"ግዳጄን ከመወጣት ውጭ ምንም አላስብም። "የሚል አስገራሚ መልስ ሰጥቷል።

ሒሮ ኦኖዳ ሀገሩ ጦሯን እንዲቀላቀል ጥሪ ስታደርግለት የ20 አመት ወጣት ነበር ። በታጂማ ዮኮ የንግድ ኩባንያ የሀንኮ ወይም ውሃን የቻይና ቅርንጫፍ ባልደረባ ነበር ። የጤና ምርመራ ተደርጎለት ብቁ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ስራውን ለቆ ጦሩን ተቀላቀለ ። በጃፓን ጦር በመቶ አለቅነት ሰለጠነ። ከዚያም ተመርጦ የወታደራዊ ስለላ ትምህርት ተከታተለ ። ወታደራዊ መረጃ እንዴት እንደሚሰበሰብና ስለ ሽምቅ ውጊያም ሰለጠነ። በታህሳስ 1944 ዓ.ም በፊሊፒንስ የሚገኘውን የሱጊ ብርጌድን ተቀላቀለ። በቅርብ አዛዦቹ የሉባንግ ምድብ የሽምቅ ውጊያ መሪ ሆነ። ለግዳጅ ከመሰማራታቸው በፊት ከክፍለ ጦሩ አዛዥ ዘንድ ቀረበው የሚከተለውን መመሪያ ተቀበሉ ። ምንም አይነት ፈተናና መከራ ቢያጋጥም የገዛ ህይወትን ማጥፋት በፍጹም የተከለከለ ነው። የሚበላ ጠፍቶ የዘንባባ ገውዝ ለመብላት ብትገደዱ እንኳ እሱን እየበላችሁ ህይወታችሁን ማቆየት አለባችሁ። በዕዝህ ሁሉም ተሰውቶ አንድ ወታደር ብቻ ቢተርፍ እንኳ እስከ መጨረሻው በጥብቅ ዲሲፕሊን የመምራት ወታደራዊ ግዴታ አለብህ። ለመቶ አለቃ ኦኖዳ ግን ይህ ወታደራዊ መመሪያ በልቡ ታትሞ የኖረ የህይወት ዘመን ቃል ኪዳን ነበር።

መቶ አለቃ ትጥቅ ፈቶ እንጂ ስለሰጠባት ክፉ ቀን ሲጠየቅ፤ ሁሉም ነገር ጨለመብኝ። ዙሪያው ገደል ሆነብኝ። በውስጤ ማዕበል ሲነሳ ተሰማኝ። የተሞኘሁ ያህል ተሰማኝ። ማኒላ እስክደርስ የሆነው ሁሉ አምኖ መቀበል ተቸገርሁ። እየቆየ በውስጤ የተቀሰቀሰው ማዕበል እየቀነሰ ሲመጣ ታወቀኝ። የሆነውን ነገር መገንዘብ ጀመርሁ። ለ30 አመታት ለሀገሬ ጃፓንና ንጉስ ጦር ስል ሳካሂደው የነበረ የሽምቅ መጠናቀቁን አምኜ ተቀበልሁ ። መቶ አለቃ ኦኖዳ በ1996 ዓ.ም ለ30 አመታት የሸመቀባትን ጓደኞቹንና የዕድሜውን ሲሶ የገበረባትን የፊሊፒንሷን ሉባንግ ደሴት ተመልሶ ጎበኘ። እገረ መንገዱንም ተሰናበታት። ዞሮ ዞሮ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከሞት አይቀርምና በ91 አመቱ በ2014 ዓ.ም ይቺን መልቲ አለም ተሰናበታት። በሀገሩ ብሔራዊ የጀግና የቀብር ስነስርዓት ተካሄደለት። ሞቱን ታዋቂ የአለማችን ብዙኃን መገናኛዎች ተቀባበሉት።

ለሀገራችንና ለሕዝባችን የምንታመንበትን ዘመን ፈጣሪ ያቅርብልን !
አሜን።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# “የካንሰር ህክምና ከፍተኛ የሆነ ትኩረትን የሚፈልግ ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ በሽታውን መከላከል የምንችልበት ቁመና ላይ ነን ለማለት አያስደፈርም“

*ዶክተር ቦጋለ ሰለሞን*

*የመጀመሪያው የካንሰር ህክምና ስፔሻሊስት*

**እፀገነት አክሊሉ**

የካንሰር ህመም በታዳጊ አገራት እየጨመረ እንደሆነ በመስኩ የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። እንደነዚሁ መረጃዎቹ ከሆነ፣ በተለይም ቅባት የበዛባቸውና ኃይል የሚሰጡ ምግቦችን አዘውትሮ መመገብ፣ እንቅስቃሴ አለማድረግ፣ ተገቢ ያልሆነ ውፍረት፣ አልኮል አብዝቶ መውሰድና የአማካኝ እድሜ ጣሪያ መጨመር ለካንሰር ህመም ተጋላጭነታችን ቀዳሚ መንስኤዎች ናቸው።

አገራት የካንሰር ህመም መከላከል እቅድና ስትራቴጂ መርሃግብሮችን ነድፈው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ዋል አደር ቢሉም ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረጉ በኩል ግን ክፍተቶች አሉ። ይህ ደግሞ ችግሩን ካለመፍትሄ እንድንጋፈጥ በማድረጉ አሁን ላይ በመላው አለም፤ እንዲሁም በአገራችን ዜጎች ለተለያዩ የካንሰር ህመሞች ተጋልጠው ይገኛሉ።

በመሆኑም ካንሰር እንዳይዘን ከተፈለገ ልናደርጋቸው የሚገቡን ተግባራት ያሉ ሲሆን፤ ቀድመን መከላከል፣ ከተያዝን በአነስተኛ ደረጃ ላይ እያለ ህመሙን ማወቅ፣ ምርመራና ህክምና ማድረግ፤ እንዲሁም፣ ህመሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ የህመምተኛውን ስቃይና የአስታማሚውን እንግልት መቀነስ የሚሉት ናቸው። እነዚህ አራት ጉዳዮችም በመንግስት ብቻ ሳይሆን፤ ታማሚውን ጨምሮ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

ህብረተሰቡ ጤናውን እንዴት መጠበቅ እንዳለበትና ተጋላጭ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን በተመለከተ ትምህርት እንዲያገኝ ማድረግም ሌላው ከመከላከያ መንገዶቹ መካከል የሚጠቀሰው ጉዳይ ነው። እንቅስቃሴ ማድረግ ከተለያዩ ህመሞች ራስን ለመከላከል የሚጠቅም በመሆኑ ከተማ ሲለማ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎችም አብረው ሊታሰቡ እንደሚገባም መታወቅ አለበት ።

በተለይም በእኛ አገር ምንም እንኳን ችግሩ ስር የሰደደ ቢሆንም የካንሰር ህክምና ባለሙያዎች እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ ይታያል። በአገር አቀፍ ደረጃ ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑት የዘርፉ ስፔሻሊስቶች ካለው የችግሩ ስፋት አንጻር ተገቢውን የመከላከል፤ ብሎም ህክምናውን በአግባቡ ለመስጠት የሚደረገውን ጥረት ውጤቱ የዘገየ እንዲሆን አድርጎታል።

ዛሬ ላይ የእነዚህን ባለሙያዎች ቁጥር ለማሳደግ በአገር ውስጥ ሳይቀር ትምህርቱ የሚያገኙበትጅ እድል የተመቻቸ ቢሆንም አሁንም በቂ የዘርፉ ባለሙያዎች አሉን ለማለት አያስደፍርም። ከእነዚህ ጥቂትና ፈር ቀዳጅ ከሆኑት የካንሰር ህክምና ስፔሻሊስት ባለሙያዎች መካከል አንዱ የዛሬ የህይወት ገጽታ አምዳችን እንግዳ የሆኑትን ዶክተር ቦጋለ ሰለሞን ሲሆኑ፤ ዶክተር ቦጋለ የመጀመሪያው የካንሰር ህክምና ስፔሻሊስት፤ እንዲሁም፣ የጥቁር አንበሳ ካንሰር ህክምና ማዕከልን ያቋቋሙ አንጋፋ የዘርፉ ባለሙያ ናቸው።

ዶክተር ቦጋለ ሰለሞን የተወለዱት ባሌ ሲሆን፣ ከጎባ ከተማ 40 ኪሎ ሜትር ወጣ ብላ በምትገኝ የገጠር መንደር ውስጥ ነው። ለቤተሰባቸው ሁለተኛ ልጅ የነበሩት ዶክተር ቦጋለ በወቅቱ ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር የገጠርን ህይወት ከመኖራቸውም በላይ ለትምህርት እንደደረሱ ያመሩት ወደ ቄስ ትምህርት ቤት ነበር። እዛም ከፊደል ጀምረው የቃል ትምህርት፣ ንባብ፣ ወንጌል፣ ዳዊት፤ እንዲሁም ቅዳሴ ተምረዋል። በወቅቱም ለትምህርት ካላቸው ፍላጎት የተነሳ፤ እንዲሁም፣ ካሉት ተማሪዎች ሁሉ በእድሜ ትንሹ እሳቸው ስለነበሩ እሁድ ሳይቀር የኔታ ጋር በመሄድ ይውሉ እንደነበር ያስታውሳሉ።

በወቅቱ ዘመናዊ ትምህርትን ለመቅሰም ወደ ከተማ ማለትም ወደ ጎባ ከተማ መምጣት ነበረባቸውና ቤተሰቦቻቸውም እንዲማሩላቸው ከነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ እዛው ጎባ ከተማ ላይ ያሉ ዘመዶችን በመለመንና ከልጃቸው ጋር በማገናኘት አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ሆነ። ነገር ግን ይህ አካሄድ ብዙም አዋጭ ስላልነበር ዶ/ር ቦጋለ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ቤት ተከራይተው ቀለብ ከቤተሰባቸው እየተጫነላቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ቻሉ።

ታዳጊው ቦጋለ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው እዛው ጎባ ከተማ “አዝማይ ደግላ” በሚባል ትምህርት ቤት ቀጠሉ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉበት የአዝማይ ደግላ ትምህርት ቤት በወቅቱ በክፍለ ሃገሩ የመጀመሪያውና ብቸኛው ሲሆን እሳቸውን ጨምሮም ብዙ ጎበዝ ተማሪዎችን ያፈራ፤ ዛሬም ድረስ አገራቸውን በተለያየ መልኩ እየጠቀሙ ያሉ ጓደኞቻቸው የተማሩበት ስለመሆኑ ይናገራሉ።

“.... ምንም እንኳን የገጠር ልጅ ብሆንም አንደኛ ደረጃም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴ ላይ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት አድርጌ ነው የተማርኩት። በዚህም ጥሩ ከሚባሉት እንደውም የደረጃ ተማሪዎች መካከል ነበርኩኝ። በዚህም ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ ይደሰቱብኝ ነበር። በተለይም ቤተሰቦቼ በትምህርቴ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ እንድደርስላቸው ከፍተኛ የሆነ ማበረታታት ያደርጉልኝ ነበር” ይላሉ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እየተማሩ አስረኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ የሙያ ምርጫ ማድረግ የቻሉት ወጣቱ ቦጋለ ለመሆን ወይም ለመማር የፈለጉት የህክምና ትምህርት ነበርና ምርጫቸውን “የጤና ተቆጣጣሪ” አደረጉ። ይህንንም ትምህርት ለመማር ወደ ጎንደር ተጓዙ።

ነገር ግን በዲፕሎማ ደረጃ ለመማር ያቀዱትን የጤና ተቆጣጣሪነት ትምህርትት አንደጀመሩ የእድገት በህብረት ዘመቻ መጣና እሳቸውም እንደ መላው የኢትዮጵያ ተማሪ ሁሉ ዘመቻውን ተቀላቀሉ።

“... እድገት በህብረት ዘመቻን የተቀላቀልኩት ከጎንደር ከተማ ነው። እንደ አጋጣሚም የደረሰኝ የዘመቻ ጣቢያ የዛሬው ሲዳማ ክልል ውስጥ ነበር። ነገር ግን ከባሌ ከወጣሁ በኋላ ለረጅም ጊዜ ቤተሰቦቼን የማየት እድሉን አግኝቼ አላውቅም። አዲስ አበባ መጥቼ የዘመቻውን አስተባባሪዎች ወደ ባሌ እንዲያዘዋውሩኝ ለመንኳቸው። እነሱም ፍቃደኛ ሆነው ወደ ትውልድ መንደሬ ዝውውር አደረኩ። በዛም ጎባ ምደብ ጣቢያ በመመደብ በአካባቢው ላይ ላሉ የጤና ሰራተኞች የቡድን አባል ሆንኩ ከቡድን አባላቶቼ ጋርም እየተዘዋወርን ለህብረተሰቡ የጤና ትምህርት አገልግሎት እንሰጥ ነበር “ይላሉ ዶ/ር ቦጋለ።

የእድገት በህብረት ዘመቻቸውን እንደጨረሱ በቀጥታ ያመሩት ያቋረጡትን የህክምና ትምህርት ለመቀጠል ወደ ጎንደር ከተማ ነበር። ጎንደር ከተማ ገብተውም ወደ ትምህርት አለሙ በመቀላቀል በእድገት በህብረት ዘመቻ ምክንያት ዳር ሳያደርሱ የተውትን ትምህርት ቀጠሉ። ለትምህርቱ ፍላጎት ስለነበራቸውም በጥሩ ውጤት አጠናቀው ለመመረቅ መቻላቸውን ይናገራሉ።

ያው ተማሪ ለፍቶ፣ ተምሮ፣ ተመርቆ መጨረሻው ስራ ማግኘት፤ በዛም በሚያገኘው ደመወዝ ለትምህርት ያወጣውን ላብ መተካት፤ አልፎም ለነገ ህይወቱ ስንቅ የሚሆኑ ነገሮችን መያዝም አይደል!? አዎ፣ ወጣቱ ቦጋለም የህክምና ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ፣ ወይም ከተመረቀቁ በኋላ በቀጥታ ያመሩት ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወደ መደባቸው የጤና ጣቢያ ሲሆን፤ ሄዶም መስራት ነበር። ግን በዚህ አገልግሎት ብዙም አልቆዩበትም።

ዶ/ር ቦጋለ ያልቆዩበትንም ምክንያት “... እንግዲህ የእድገት በህብረት ዘመቻ ዘርፈ ብዙ መልክ ያለው ነው። እኔም በሙያዬ ላገለግል በሄድኩበት አካባቢ ላይ ሌሎች ግብረ ሰናይ ደርጅቶች ደግሞ ፈንጣጣን (Smallpox) የማጥፋት ስራ ይሰሩ ነበር። በወቅቱ እኔም ከእነዚህ አካላት ጋር የመስራትን እድል አግኝቼ ነበርና



አውቃቸዋለሁ፤ ያውቁኛልም። ዘመቻው ተጠናቆ እኔም ወደ ትምህርቴ ተመልሼ ተምሬ፤ ተመርቄ ስራ እየሰራሁ ባለሁበት ወቅት አብሬያቸው እንድሰራ ጠየቁኝ። የጠየቁት እኔን ብቻ አይደለም፤ ጤና ጥበቃንም ነበር። የጤና ጥበቃም ፍቃድ ስለሰጠኝ የጤና ጣቢያ ስራዬን አልቀጠልኩበትም” በማለት ነው የገለፁት።

ጤና ጥበቃም ስለፈቀደ ችግሩን የማስወገድ ስራ ላይ መግባታቸውን ይናገራሉ።

ምንም እንኳን ወቅቱ ፋንጣጣ ከኢትዮጵያ እየወጣ ያለበት ወቅት ቢሆንም፤ አጋዴን አካባቢ ግን ችግሩ ስለነበር እሱን ለማስወገድ ነው አብረው እንዲሰሩ የተጠየቁት። ዶክተርም ባላቸው የስራ ልምድ ፈንጣጣን ለማጥፋት የሚደረገውን ጥረት አጋዴን ድረስ በመሄድ ሊወጡ ተቋሙን ተቀላቀሉ። ስራውንም በሚገባ ሰርተው ፈንጣጣም ዳግመኛ ኢትዮጵያ ላይ እንዳይከሰት አደርገው ግዳጃቸውን በሚገባ ከተወጡ በኋላ ጉዟቸውን ወደ አዲስ አበባ ስለማድረጋቸው አጫውተውናል።

“.... በወቅቱ እድገት በህብረት ላይ የሰራሁት ስራ ፈንጣጣን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት ላይ እንድሳተፍ አስመረጠኝ። በእርግጥ እኔም በዚህ ስራ በመሳተፌ በጣም ደስተኛ ነበርኩ። ጥሩ ክፍያ ከአበልና መኪና ጋር ሰጥተውኝ በጥሩ ሁኔታ ነው ስራውን የሰራሁት። አጋጣሚውም የተሳካ ስለነበር ስራውን በአጭር ጊዜ ለመጨረስ በቅተናል” በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

ፈንጣጣን የመዋጋት ስራው እንደተጠናቀቀ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሜዲካል ትምህርት ቤት ነበር ያቀኑት። በዛም ለጠቅላላ ሀኪምነት የሚያበቃውን የህክምና ትምህርታቸውን (ጀነራል ፕራክቲሽነር) ለሰባት ዓመታት ያህል ለመከታተል ገቡ። በወቅቱ መልካም የሚባል የትምህርት ጊዜን ማሳለፋቸውንና ከብዙ ምርጥ መምህራን እስከ ዛሬ ድረስ የሚያስታውሱትና የሚጠቀሙበት እውቀትንም ስለማግኘታቸው ይመሰክራሉ ።

የህክምና ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁም በቀጥታ ስራ የጀመሩት የኢትዮጵያ አየር ሃይል ውስጥ ሆነ። እዛም በነበሩበት ወቅት ሃኪምም፣ አባልም ለመሆን የቻሉት ዶ/ር ቦጋለ በዚህም እስከ ሻምበልነት ድረስ የዘለቀ ወራደራዊ ማዕረግን ለማግኘት በቅተዋል።

የህክምና ትምህርት ”በቃ፣ ተምሬያለህ፤ እዚህ ላይ ይበቃኛል” የሚባል አይደለም የሚሉት ዶክተር ቦጋለ ተምረው የህክምና ሙያን ቢያገኙም ጥሩ ስራ ኖሯቸው፤ ህዝባቸውን እያገለገሉ የነበረ ቢሆንም፤ ይበልጥ ተምረው፣ አውቀው፤ በተለይም ደግሞ አንድ የህክምና አይነትን በደንብ አጥንተው አገርና ህዝብ የጣለባቸውን ሃላፊነት ለመወጣት በማሰብ እንቅልፍ አልተኙም። ይህንንም ህልማቸውን ለማሳካት የአየር ሃይል ስራቸውን አቋርጠው ዳግም ትምህርትቸውን ለመቀጠል ወሰኑ። በዚህም ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የህክምና ትምህርት ቤት ተመልሰው ገቡ።

“... በወቅቱ እድለኛ ነኝም ማለት እችላለሁ፤ የህክምና ትምህርቴን ተምሬ እንደ ጨረስኩ አየር ሃይል ውስጥ ስራ ተመደብኩ። እዛም ከተራ ሰራተኝነት ጀምሮ አባል እስከ መሆንና ማዕረግም እስከ ማግኘት ደረስኩ። ቀጥሎም ትምህርቴን ”ስፔሻላይዝድ” አደርጋለሁ ብዬ ስጠይቅ መስሪያ ቤቴ ”ትችላለህ” ብሎ ደመወዝ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

እየከፈለኝ ልማር ትምህርት ቤት ገባሁ” በማለት ሁኔታውን ወደ ኋላ ያስታውሳሉ።

ነገር ግን በወቅቱ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ባለበት ጊዜ ሆስፒታሉ የካንሰር ህክምናን ኢትዮጵያ ውስጥ ለማቋቋም የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ከጤና ጥበቃ ጋርም እቅድ ይዞ ስለነበር ከነበሩት የስፔሻላይዜሽን (በአንድ የህክምና (ለምሳሌ የዐይን) ዘርፍ ላይ የበለጠ መሰልጠን) ተማሪዎች መካከል እርሳቸው የመመረጥ እድልን አገኙ።

“... በወቅቱ እኔ ምንም ያማውቀው ነገር አልነበረም። ነገር ግን፣ ሆስፒታሉ ከጤና ጥበቃ ጋር ባዘጋጀው እቅድ መሰረት የካንሰር ህክምና ማዕከል ሊከፈት ሆነ። ለዚህ ደግሞ ሃኪም ትሆን ዘንድ ለትምህርቱ፤ እንዲሁም ለስራው ተመርጠሃል ተባልኩ። እኔ በወቅቱ ያስተምረኝ የነበረው አየር ሃይል ስለነበር፤ ይህ ነገር አይሆንም፣ እቸገራለሁ አልኩና መልስ ሰጠሁ። አይ አንተ ፈቃደኛ ሁን እንጂ ፕሮጀክቱ አገራዊ ስለሆነ ቀጣሪዎችህን እናነጋግራለን፤ እንጨርሳለን አሉ፤ አይ እንደዛማ ካደረጋችሁልኝ ለእኔ ትልቅ እድል ነው በማለት ፈቃደኝነቴን ገለጽኩ” ይላሉ።

በወቅቱ አየር ሃይል የጉዳዩን አስፈላጊነት ወደ ፊትም ለአገር የሚኖረውን ተስፋ በማየት ችግር የለውም፤ ይሰልጥን በማለት ፍቃድ ሰጣቸው። እርሳቸውም በካንሰር ህክምና ላይ ስፔሻላይዝድ ለማድረግ ጉዟቸውን ወደ ግብጽ ዋና ከተማ፣ ካይሮ አደረጉ። በወቅቱ ካይሮ በመሄድ የካንሰር ህክምና ስልጠናን የወሰዱት ብቸኛው ሰውም ሆኑ። ከዛ በኋላ ግን ነጻ የትምህርት እድል በመስጠቱ ሌሎች ሃኪሞች፣ ቴክኖሎጂስቶች፣ ሜዲካል ፊዚስቶች፣ መሰልጠናቸውን ይናገራሉ።

ካይሮ ትምህርታቸውን እየተማሩ ብዙ ነገሮችን ”አገሬ ላይ ቢሆን” ብለው የሚመኟቸውን የህክምና ጥበቦች፤ በተለይም ደግሞ በካንሰር ህክምና በኩል እንዳዩ ይናገራሉ። ትምህርታቸውን በተያዘላቸው ጊዜ ሰሌዳ መሰረት አጠናቀው ወደ አገራቸው እንደተመለሱም በቀጥታ ያመሩት ወደ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የካንሰር ህክምና ክፍል ነበር። ወደ’ዛ ያምሩ እንጂ በወቅቱ የመጀመሪያው ሃኪምም ሆነው የሰለጠኑት እሳቸው ብቻ ናቸው። የህክምና ማዕከሉም ገና አልተደራጀም ነበር። ስለዚህ ህክምና ክፍሉን ከማደራጀት ጀምሮ ህክምናውን መስጠትም የእርሳቸው ሃላፊነት ሆነ። የተሰጣቸውንም ሃላፊነት በአግባቡ በመወጣት ብቸኛው ሀኪም እሳቸው ሆነው የህክምና ክፍሉ እውን ሆነ።

“.... በወቅቱ በሽታው እንደአሁኑ ስር የሰደደና ብዙ ሰዎች ላይ የሚታይ ባይሆንም በአገራችን የካንሰር ህመምተኞች ነበሩ። ህክምናው ግን አይታወቅምም፤ አይሰጥምም ነበር። በሌላ በኩልም በሰዎች ዘንድ ስለ ህመሙ የነበረው ግንዛቤ አናሳ ስለሆነ ህመሙ የሚታይባቸው ሰዎች ወደ ህክምና ተቋም የሚመጡት ዘግይተው፣ በሽታው ወደ መላ ሰውነታቸው ከተሰራጨ በኋላ ነበር። ይህ ደግሞ የተሟላ ህክምናም ካለመኖሩ ጋር ተደማምሮ ብዙዎቹ ቀናቸውን እየጠበቁ ያልፉ ነበር” ይላሉ ያንን ክፉ ጊዜ ከሙያ አኳያ እያስታወሱ።

ወደ ካንሰር ህክምና ትምህርት ሲገቡ የፈቀደላቸው አየር ሃይል አሁን በቃ በተማረበት ሙያ ያገልግል በማለት ሙሉ በሙሉ ለቀቃቸው። ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲዘዋወሩም መልካም ፍቃዱ ሆነ። በመሆኑም ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ገብተው የህክምና ቦታውን መምረጥ፣ ቤቱን ማሰራት፣ የህክምና ግብዓቶችን፤ እንዲሁም መድሃኒት እንዲሟላ ማድረጉ ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራታቸውን ቀጠሉ።

“... ከትምህርት ከመጣሁ በኋላ የህክምና ስራዬን ከመስራት ባሻገር ዋና ስራዬ የነበረው የህክምና ቤቱን ማስገንባት፣ የህክምና እቃዎችን ማሟላት ነበር። ይህንንም በሚገባ በመስራት የህክምና ማዕከሉ መስራት በሚችልበት ቁመና ላይ እንዲገኝ አድርጌዋለሁ”በማለት ስራቸውንና በመስራታቸው የተሰማቸውን እርካታ ይገልፁታል።

ይህንን ስራም በሚገባ የተወጡት ዶ/ር ቦጋለ ቤቱ ተሰርቷል፤ እቃው ከሞላ ጎደልም ቢሆን ተሟልቷልና በቃ ብለው አልተቀመጡም። ይልቁንም ህመምተኞች ከመላው አገሪቱ የሚመጡ ከመሆናቸው አንጻር፣ እንዲሁም በሽታው ስለሚጎዳቸውም አብዛኞቹን ስቃያቸውን ከማስታገስ የዘለለ ህክምና መስጠት አለመቻሉም በጣም ይረብሻቸው ነበር። ይህ እንዳለ



ከዚህ ቀደም ካንሰር ያደጉ አገራት በሽታ ሆኖ ቆይቷል። ዛሬ ላይ ግን ያ ታሪክ ሆኖ ቀርቷል። እንደውም፣ የእኛ የደሀ አገራት ትልቅ ችግር ሆኖ ነው ያለው። በመሆኑም በሽታው ከዚህ በኋላም ቢሆን በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የሚሄድ በመሆኑ መጠንቀቁ በጣም አስፈላጊ ነው

ሆኖ ደግሞ በሽታው እንደታየባቸው ለመጡት ሰዎች ከኦፕሬሽን ጀምሮ የጨረር ህክምናን ሰጥቶ ተገቢውን ድጋፍ እስከማድረግ የደረሰ ከፍተኛ ስራንም ያከናውኑ ነበር ።

“... አሁን ላይ እኛ የካንሰር ሃኪም ሆነን ስራ ከጀመርንበት ጊዜ ጋር የማይነጻጸሩ ብዙ ለውጦች አሉ። በወቅቱ እንዳልኩሽ በበሽታው ላይ ህብረተሰቡ የነበረው አረዳድ ፈጥኖ ወደ ጤና ተቋም መሄድ ላይ የነበረው ችግር፤ ከዛም ወደ ጤና ተቋም ሲመጣ ህክምናው በአንድ ሆስፒታል በጥቂት ባለሙያዎች ብቻ መሰጠቱ ከፍተኛ የሆነ ችግር ነበር። ዛሬ ላይ ግን ብዙ የተሻሻሉ ነገሮች ከመኖራቸውም በላይ አሁን ህክምናው በአብዛኞቹ የግልና የመንግስት ሆስፒታሎችም ይገኛል። ለእኔ ይህንን ማየቴ ደግሞ ትልቅ ነገር ነው። ትልቅ ደስታ ነው የሚፈጥርብኝ” ይላሉ።

ይህም ቢሆን የበሽታው መስፋፋት፣ ፍጥነትና ሌሎችም ነገሮች ተደማምረው፤ እንዲሁም አለም የደረሰብትን የቴክኖሊጂ ደረጃ ሲያዩት አገራችን ገና ብዙ መስራት ይቀራታል ይላሉ። በመሆኑም የካንሰር በሽታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ እንጂ የሚቀንስ ባለመሆኑ ፖሊሲ አውጪዎችም፤ ጤና ሚኒስቴር አካባቢ ያሉ ሰዎችም ትልቅ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ስለመሆኑም አበክረው ይናገራሉ።

እንደው የችግሩን ውስብስብነትና ህመሙ ከሚያስከትለው ከፍተኛ ስቃይ አኳያ ሲያዩ፤ እንዲሁም ሰዎች ሲረዱሲ ቆይተው ህይወታቸው ሲያልፍ ”ምነው ባልተማርኩ” አላሉም ነበር? በማለት ላነሳንላቸው ሃሳብም፤

“... አይ እንደውም ካይሮ ትምህርት ላይ በነበርኩበት ጊዜ በአገሪቱ ያለው የህክምና አማራጭ፣ የመድሃኒቱ ብዛት ሰዎች በበሽታው ላይ ትልቅ ግንዛቤ ያላቸው በመሆናቸው ምልክት እንዳዩ መጥተው፣ ታክመውና ድነው ሲሄዱ ሳይ ’መቼ ነው እኔም አገር ይህን መሰሉ የህክምና አሰጣጥ ተፈጥሮ እንደ ካይሮ ነዋሪዎች ሁሉ ኢትዮጵያዊያንም ከህመማቸው ድነው የማይበትን ቀን?’ በማለት ነበር የምመኘውም። ምንም እንኳን የወገኖቻችን ችግር ሰፊና ውስብስብ ቢሆንም የግንዛቤ ችግሩም አለ። አሁን ላይ ህክምናው እየተሰጠ ብዙዎችም እየዳኑ መሆኑን ሳይ ’እንኳንም ተማርኩት’ ነው የምለው” ይላሉ።

ዶክተር ቦጋለ በስራ ምክንያት በበርካታ የአፍሪካ፣ የአውሮፓ እንዲሁም የእሲያ አገራት ተዘዋውረዋል። በእነዚህ አገሮች ደግሞ ብዙ ተሞክሮዎችንም ቀስመው ነው የመጡት። ካዮዋቸውና እርሳቸው አስፈላጊና ጥሩ ነው ከሚሉት ነገር አንዱ ደግሞ ሰዎች ለካንሰር ህመም እንዳይዳረጉ ቅድመ መከላካል ላይ መስራቱን ነው። ሌላው በሽታው በአነስተኛ ደረጃ ላይ እያለ ተገኝቶ ማከመን ነው። እነዚህን ልምዶች ወደ አገራችን ለማምጣት የህክምና ማዕከላቱ ጉዳይ በዚህ ደረጃ ፈጣንና ቀልጣፋ ህክምናን ለመስጠት ያስችላል ባይባልም ቅሉ፤ ወደ ፊት ግን ሌሎች አገራት በሚሄዱበት መንገድ ተጉዘን ወገናችንን ከበሽታው እንታደጋለን የሚል ተስፋ አላቸው።

“... እኛም እንደሌሎቹ አገሮች ካንሰርን አክመን የምንድንበት ጊዜ እንደሚመጣ እርግጠኛ ነኝ። አሁንም ከበፊቱ የተሻለ ደረጃ ላይ ነን ብዬ ለመናገር እደፍራለሁ” ይላሉ።

ዶክተር ቦጋለ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የካንሰር ስፔሻሊስት ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚገኘውንም የካንሰር ህክምና ማዕከል አደራጅተው ለስራ ያበቁ ምሁር ናቸው። ከዚህ ጎን ለጎንም የህክምና ባለሙያ ከሆኑት ባለቤታቸው ጋር ትዳር መስርተው የሁለት ወንዶችና የአንዲት ሴት ልጅ አባትም ናቸው።

በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ የእናትና አባታቸውን ፈለግ ተከትለው ሶስቱም ልጆቻቸው የህክምና ባለሙያ በመሆን ነው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙት። ዶ/ር ቦጋለ በአሁኑ ወቅት የመጀመሪያ ልጃቸው ትዳር መስርቶ የልጅ ልጅ አሳይቷቸዋል።

**በካንሰር ህክምናው ዘርፍ ቢሆን .....**

የካንሰር ህክምና ከፍተኛ የሆነ ትኩረትን የሚፈልግ ነገር ነው። አሁን ባለው ሁኔታ በሽታውን መከላከል የምንችልበት ቁመና ላይ ነን ለማለት አያስደፈርም። የህክምና አገልግሎቱ ዝቅተኛ ከመሆኑ አንጻር ህመምተኞቻችንን እንኳን በአግባቡ የሚገባቸውን ህክምን እንዲያገኙ ማስቻል ላይ አልደረስንም።

ከዚህ ቀደም ካንሰር ያደጉ አገራት በሽታ ሆኖ ቆይቷል። ዛሬ ላይ ግን ያ ታሪክ ሆኖ ቀርቷል። እንደውም፣ የእኛ የደሀ አገራት ትልቅ ችግር ሆኖ ነው ያለው። በመሆኑም በሽታው ከዚህ በኋላም ቢሆን በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የሚሄድ በመሆኑ መጠንቀቁ በጣም አስፈላጊ ነው።

በነገራችን ላይ ያደጉት አገራት ከእኛም በፊት ህመሙን ስለሚያውቁትና በቂ ዝግጅትም ያደረጉ በመሆናቸው አክሞ ማዳኑ ለእነሱ ከባድ አልነበረም። እኛ ግን የህክምና ሁኔታችን በቂ ካለመሆኑ አንጻር፤ እንዲሁም፣ ክልሎችም ላይ በበቂ ሁኔታ ያላዳረስነው የህክምና አሰጣጥ ሁኔታ ስላለ፤ ሰዎችም ህመሙ ሲጠናባቸው ስለሆነ ወደ ህክምና ተቋሚት የሚመጡት አክሞ ማዳኑ ፈታኝ ይሆናል።

ወደ ፊት ግን እነዚህ ሁኔታዎች እየተሻሻሉ በአነስተኛ ደረጃ ህመሙን አግኝቶ ማከሙም ሆነ መከላከሉ ላይ የሚሰራው ስራ እየተሻሻለ ከሄደ፤ በካንሰር የሚሞቱ ህሙማን ቁጥር እየቀነሰ እንደሚሄድ ተስፋ አለኝ። ያደጉት አገራት ተሞክሮም የሚያሳየው ይህንን ነው። በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ከምስራቅ አፍሪካ ጥበባትና ባህል ፌስቲቫል ምን እንጠብቅ?

**ዳግም ከበደ**

የምስራቅ አፍሪካ ጥበባትና ባህል ፌስቲቫል በተያዘው ሰኔ ወር በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል። ይህን መሰል ሁነት በቀጠናው ያለውን ባህላዊ፣ ኪነ ጥበባዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና አጠቃላይ ማህበራዊ ትስስር እንደሚያጠናክረው ደግሞ ባለሙያዎች ይናገራሉ። በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ በሚመለከታቸው አካላት አስተናባሪነት በአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ የሚዘጋጀው ፌስቲቫሉ በርካታ ሁነቶችን እንደሚያስተናግድ ይጠበቃል። ይህ ሁነት ላለፉት ሶስት ወራት በመንግስት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ዝግጅት ሲደረግበት ቆይቷል።

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የተለያዩ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፣ ለመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችም የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ቀደም ሲል አካሂዷል። በጉዳዩ ላይ ከፍተኛ የፌዴራል መንግስቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት መግለጫ ሰጥተውበታል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ ‹‹የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ወንዞች፣ መልክአ ምድር፣ ብዝኃ ሕይወት ያስተሳሰሯቸው ፤ ተመሳሳይ የዘር ግንድ፣ የጋራ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ባህላዊ እሴት ያላቸው ሕዝቦች የሚኖሩበት ቀጠና ቢሆንም፣ የአውሮፓዊያን ቅኝ ገዥዎች በፈጠሯቸው ድንበሮች ምክንያት ሳይወዱ በግድ ተነጣጥለው እንዲኖሩ ተደርገዋል። ›› ሲሉ ገልጸው፣ ‹‹ ‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ወዳጅ፤› እንደሚባለው ሀገራችን ኢትዮጵያ ጎረቤት መር በሆነ ግንኙነት ለሺ ዘመናት የዘለቀውን የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ግንኙነት በጥበብና በባህል በማስተሳሰር እና በማጎልበት በቀጣይ ቀጠናውን በኢኮኖሚ ለማስተሳስር ና የቀጠናውን ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል መሰረት የሚጣልበት ፌስቲቫል አዘጋጅታለች ብለዋል።

የምስራቅ አፍሪካ የጥባባት እና የባህል ፌስቲቫሉን በይፋ በማስተዋወቅ መልዕክት ያስተላለፉት የኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በበኩላቸው የምስራቅ አፍሪካ የጥበባትና የባህል ፌስቲቫል ለቀጠናው ሰላም፣ የህዝቦች ትስስር እና ልማት ወሳኝ መሆኑን አስታውቀዋል።

የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የባህል ዲፕሎማሲን በትኩረት መከወን ይገባል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ ‹‹በውጭ ጉዳያችን በኩል ዋናው የምንረባረብበት የትኩረት ማዕከላችን የጎረቤት ሀገራትን መሰረት ያደረገ ግንኙነት መፍጠር ነው›› ብለዋል። ‹‹እንዳለመታደል ሆኖ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና የሚታወቀው በጦርነት፣ በድርቅ፣ በርሃብ እና በስደት ነው። ይህንን ገፅታ መቀየር የምንችለው ሕዝብና ሕዝብን በጥበባትና በባህል በማስተሳሰር ተፈጥሮ ያደለችንን ፀጋ ተጠቅመን ቀጠናውን ስናለማ ነው›› ሲሉ አስገንዝበዋል። ይህን ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር ያለመ ፌስቲቫል በዚህ በያዝነው ሰኔ ወር ለማዘጋጀት ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ መሆኑንም ይፋ አድርገዋል።

በቅርቡም የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዝግጅቱ ላይ በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል። ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳ በፌስቲቫሉ የኢትዮጵያ ክልሎች፣ የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የባህልና ኪነጥበብ ስራዎቻቸውን እንደሚያቀርቡ ጠቅሰው፣ የባህልና የጥበባት ሁነቱ የቀጠናው ሀገሮችና የአፍሪካ ህዝቦች፣ ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ እድል እንደሚሰጥ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ ከሚዘጋጁ ተመሳሳይ ሁነቶች ላይ የገበያ ድርሻ እንዲኖራት ምቹ ሁኔታ አንደሚፈጥርም ጠቁመዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ፌስቲቫሉ በተለይ በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ረገድ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ከትርኢቱ ባሻገር አንድ አፍሪካን ለመፍጠር እየታሰቡ ካሉት ሁነቶች አንዱ ጅማሮ መሆኑን ገልጸዋል። ባህልና ጥበብን በመጠቀም የቀጠናውን ህዝቦች እርስ በርስ የበለጠ ለማቀራረብና ለማጠናከር ወቅታዊ ፓለቲካዊ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ፣የገጽታ ግንባታ ለማካሄድ ያስችላል ይላሉ።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አለማየሁ ጌታቸው ለዝግጅት ክፍላችን የፌስቲቫሉን አስፈላጊነትና ዋንኛ አላማ ሲገልፁ እንዳሉት፤ አጠቃላይ ዓላማው ባህል እና ጥበባትን በመጠቀም የሚዘጋጀው ፌስቲቫል የቀጠናውን ህዝቦች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነትን ማጎልበት ነው። በዝርዝር ደግሞ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ባህሎቻቸውን እንዲያስተዋውቁና ማህበራዊ ትስስራቸው እንዲጎለብት በማድረግ ዘላቂ ቀጠናዊ ሰላም መፍጠር፣ በሀገራት መካከል የብዝሃ ባህልና አብሮነት የተመለከቱ የልምድ ልውውጦች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣ የቀጠናው ሀገራት ህዝቦች የባህል መገለጫዎች እና የኪነጥበብ ስራዎችን በመጠቀም ያለንን የባህል ሀብት ለገጽታ ግንባታ እንዲሆኑ ማስቻል ነው። ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ጋር ያለንን የመሰረተ ልማት ትስስር ማጠናከርና የኢንቨስትመንት ማስፋፋት፤ በባህልና በኪነ ጥበብ ምርትና አገልግሎት ዘርፍ በአምራቾችና በተጠቃሚዎች መካከል ቀጣይነት ያለው የጠናከረ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርና የገበያ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፤ የዘርፉን ባለሙያዎች የእውቀትና ክህሎት እንዲሁም ተግባራዊ ልምምድ የሚገኙበትን ዕድል በመፍጠር አቅማቸውን ማሳደግ የሚሉትም የፌስቲቫሉ ፋይዳዎች ናቸው።




“የምስራቅ አፍሪካ የጥበባትና ባህል ፌስቲቫል በውስጡ አራት ዋና ዋና መርሀ-ግብሮችን ያካተተ” የሚሉት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተሩ፤ እነርሱም ዐውደ ጥናት፣ ዐውደ ርዕይ፣ የኪነ ጥበባት እና ስፖርታዊ ዝግጅቶች እንደሆኑ ይናገራሉ። በሁነቱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በርካታ ባለድርሻ አካላት እና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ በመጥቀስም እንዲህ ዓይነቱ ሁነት ከእቅድ ጀምሮ ቅድመ ሁነት፣ ጊዜ ሁነት እና ድኅረ ሁነት ወቅቶች ለሚከናወኑ ሥራዎች ሰፊ ጊዜ፣ ከፍተኛ በጀት፣ በርካታ የሰው ሀብት እና ቁሳቁስ እንደሚጠይቅ ይገልፃሉ። ይህንኑ መሰረት በማድረግ በተቀናጀ ዕቅድ እና አመራር የታለመለትን ውጤት ለማምጣት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ዝግጅቶች እንደሚቀርቡ ያስረዳሉ።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ አውደ ጥናቱ የምስራቅ አፍሪካን ትስስር ማጠናከር “Cultivating East African Integration” በሚል ስያሜ ይካሄዳል። በቀጠናው ህዝቦች ጥቅም ላይ የሚውሉ የጋራ ባህላዊ ሀብቶች፣ እሴቶች፣ ቋንቋ እና ኪነ ጥበብ ለጋራ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትና ተጠቃሚነት ባላቸለው ፋይዳ ላይ ያተኮሩ ጥናታዊ ፅሁፎች የሚቀርቡበት እና ልምድ የሚቀሰምበት መድረክ ነው።

የዕደ ጥበባት ዓውደ ርዕዩ ደግሞ የምስራቅ አፍሪካውያን የባህል ተምሳሌት እና መገለጫ “East Africans Cultural Symbol and Expression” በሚል ስያሜ የሚካሄድ ነው። ይህ ዝግጅት የባህል መገለጫ የሆኑ ምግቦች እና መጠጦች፣ የእደ ጥበብ ምርቶች፣ የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ስራዎች ለዕይታ የሚቀርቡበት መሆኑንም ገልጾልናል።

የመጻሕፍት ዐውደ ርዕይም ምስራቅ አፍሪካ ታንብብ “Let East Africa Read” በሚል ስያሜ ይካሄዳል። ይህ ዝግጅት በየሀገራቱ የታተሙ ታሪካዊ መጻሕፍት ለዕይታ የሚቀርቡበት ነው።

የሙዚቃ ፌስቲቫልም ይካሄዳል። ይህም የምስራቅ አፍሪካ ሙዚቃ ቃና!! ‘’Rhythms of the East Africa’’ በሚል ስያሜ የሚካሄድ ነው። የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን ባህላዊ ሙዚቃዎች፣ ትርዒቶች፣ ሰርከስ፣ ዳንስ፣ ኮሜዲ እና ስነ ጽሁፍ የሚያሳይ ልምድ የሚቀሰምበት ድግስ በመድረክና በተለያዩ የዕይታ ቦታዎች ለታዳሚ ይቀርብበታል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የፊልም ፌስቲቫል ይካሄዳል። ፌስቲቫሉ ሀገራትን ማስተዋወቅ እና ማገናኘት! “Promoting and bridging the nations” በሚል ስያሜ ነው የሚካሄደው። የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ የሚያስተሳስሩ የባህል ትስስርን የሚያሳዩ ስለቀጠናው የሚናገሩ ታሪካዊ ፊልሞች ለዕይታ ይቀርባሉ።

የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ፌስቲቫል የሚካሄድ ሲሆን፣ የምስራቅ አፍሪካ ቀለም “East African Colors” በሚል ስያሜ የሚካሄድ ነው። የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ሰዓሊያን ስራቸውን በተለያየ የዕይታ ቦታዎች ለታዳሚ የሚያቀርቡበት ነው።

## ባህልና ቀጠናዊ ትስስር

ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፤ ባህልና ጥበባት ሰዎች እርስ በርስ በሚኖራቸው ግንኙነት እና ማኅበራዊ መስተጋብር ለዘመናት ያፈሯቸውን እሴቶች እና የአኗኗር ዘይቤዎች ለአካባቢያቸው እና ለሌሎች ህዝቦች የሚያጋሩበት እና የሚያስተዋውቁበት አንደኛው መሳሪያቸው ነው። በመሆኑም ባህልና ጥበባት ለሀገረ መንግስት ግንባታ እና ማህበራዊ ሀብት ክምችት (Social Capital development) ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ በተለያየ ጥናቶች የተረጋገጠ ነው። በመሆኑም ብዝሃ ባህል እና እሴቶች ለተጀመረው የሀገረ መንግስት ግንባታ ያላቸውን ሚና ለማጎልበት የጥበባትና ባህል ፌስቲቫሎችን ማዘጋጀት እና መሰል ሁነቶች በስፋት በማቀድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ጥበብ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲሁም ለህዝቦች ትስስር ገር ሀይል (soft power) በመሆኑ ይህንኑ ፀጋ በመጠበቅ፣ ማልማትና ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

የክፍል አህጉራዊ አደረጃጀቶች እና ኢኒሼቲቮች ማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ እድገትን ለማፋጠን በጎ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ይታመናል። ይህንኑም ዳዊት አለምነህ (2007) Economic Integration in East Africa: The Case of Ethiopia and Kenya’ በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት በምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል የሚኖር በቀጠናዊ የፀጥታ እና ደህንነት ጉዳዮች እንዲሁም የኢኮኖሚ መሰረቶች ማለትም በኃይል አቅርቦት፣ በመንገድ መሰረተ-ልማት እና ንግድ የሚኖር ግንኙነት ለቀጠናዊ ትስስር ወሳኝ መሆኑን አመልክተዋል።

በተጨማሪም East African Outlook (2019) በአፍሪካ ልማት ባንክ ቡድን አዘጋጅነት “የቀጠናዊ ትስስር ፓለቲካል ኢኮኖሚ” በሚል ባወጣው ጽሁፍ እንደተመለከተው፤ የቀጠናው ሀገራት በንግድ፣ መንገድ እንዲሁም በቴሌኮም አገልግሎቶችና ኃይል አቅርቦት በመተሳሰር ለአጠቃላይ ዕድገት መጠቀም የሚችሉበትን ዕድል እንዳልተጠቀሙ አሀዛዊ መረጃዎችን ጭምር አስደግፎ ያትታል። በቀጣይም ሁለንተናዊ የመሰረተ-ልማት ትስስር እና ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ያላቸው የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥና ተግባራዊ በማድረግ ተወዳዳሪና እድገት ያለው ምጣኔ ሀብት በቀጠናው መገንባት እንደሚገባ ምክረ-ሀሳብ አቅርቧል።

በሀገራት መካከል በጋራ ጥቅም ላይ የሚመሰረት የመሰረተ-ልማት ትስስርን ለማምጣት የሚደረግ ጥረት በህዝቦች መካከል በሚደረጉ የባህል እና ጥበባት ስራዎችና መድረኮች ቢታገዝ የበለጠ ውጤታማ ሊሆን ይቻላል። ይህንንም ከምስራቅ አፍሪካ ህዝቦች ቀደምት ታሪካዊ፣ ስነ-ምህዳራዊ ተመሳስሎና ተቀራራቢ ባህል አንጻር የህዝቦችን የጋራ ማንነት የሚያጎለብቱ የባህል ፌስቲቫሎች በማዘጋጀት ለቀጠናዊ ትስስር የሚውሉበትን ስልት በመቀየስ ለቀጠናው ዘላቂ ሰላምና ልማት እንዲውል መጠቀም ያስፈልጋል። የዲፕሎማሲ ተልዕኮን ወደ ተግባር በመቀየር የህዝቦችን ማህበራዊ ትስስር ለማጠናከር ባህል ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

በተጨማሪም በሀገራችን መሰል ኩነቶች መዘጋጀታቸው በዘርፍ ተሻጋሪ ጉዳዮች ላይ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ለመሆኑ በርካታ ማሳያዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ። የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም በሚወሰዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ በተፈጥሮ ሀብት ስራዎች እና የተለያየ የቢዝነስ ተቋማት ከሀገራችን ውጪ በቀጠናው ሀገራት የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸውን የገበያ ድርሻ እና ተሳትፎ በማጎልበት የምጣኔ ሀብትና የንግድ ትስስርን ለማጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

## የፌስቲቫሉ ለምስራቅ አፍሪካ ያለው ፋይዳ

እንደ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተሩ ገለፃ ፤ በኢትዮጵያና እና በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ የጥበባት እና ባህል ፌስቲቫል መዘጋጀቱ ከአጭር ጊዜ አንጻር ማለትም እስከ አንድ ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ አንጻር ከፍተኛ አበርክቶ ይኖረዋል። በሀገራችን እና በቀጠናው ሀገራትና ህዝቦች መካከል በሚፈጠረው መስተጋብር በቀጠናው ህዝቦች መካከል እርስ በእርስ የበለጠ መቀራረብና መተማመንን በማጠናከር በሀገራችን እንዲሁም ጥበብና ባህልን በመጠቀም በምስራቅ አፍሪካ የሚስተዋለውን ወቅታዊ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ለማሻሻል እና በጎ ያልሆኑ እይታዎች ለማለዘብ የሚረዱ የገጽታ ግንባታ ስራዎች ለመስራት ያስችላል።

“የመድረኩ መዘጋጀት በርካታ ማህበራዊ ፋይዳዎች አሉት የሚሉት አቶ አለማየሁ፤ ህዝቦችን ከማቀራረብና ከማስተሳሰር አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ይላሉ። በቀጠናው ያሉ ህዝቦች ካላቸው የመልከዓ ምድር፣ የባህል ፣ ቋንቋ እና የስነ ልቦና ተዛምዶ አንጻር ህዝቦች እርስ በርስ የበለጠ እንዲተዋወቁ፣ እንዲደናነቁ እና ግንዛቤ እንዲጨብጡ የሚያስችሉ ዝግጅቶች የሚቀርቡበት መሆኑን ይገልጻሉ። ይህም በጥበባትና የስፖርት ዝግጅቶች ደስታና ተዝናኖትን ከመፍጠር ባሻገር ውስጣዊ ግንኙነት ከማጠናከር አልፎ ነጻና አሳታፊ የባህል እና ጥበባት አቅርቦት እንዲኖር ያግዛል። በተጨማሪም ሲምፖዚየምና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች፣ የተሞክሮ መለዋወጫ መድረኮች መኖራቸው ለተማሪዎች ፣ ተመራማሪዎች፣ ለትምህርት ተቋማት፣ ምርምርና ፈጠራ በማጎልበት ለዘርፉ ባለሙያዎች ዕውቀትና ተግባራዊ ልምድ በመፍጠር የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለመስራት ያስችላል ብለዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

# የታሪክ ነጋሪው ታሪክ


« . . . የሰማይ መላእክት የምድር ሠራዊት ሊያስቡትና ሊያውቁት ይቻላቸው ዘንድ በዚህ በዛሬ ቀን ቸር እግዚአብሔር በመከራችሁ ስመገኘት ስላበቃኝ በሰው እና የሚነገር ምስጋና የሚበቃ አይደለም . . . »

ቀ. ኃ. ሥ.

አዲስ ፡ ዘመን

« . . . ከማናቸውም አስቀድሜ ለሁላችሁ ልንገራችሁና ልትረዱት የምፈልገው ይህ ቀን ላዲሲቱ ኢትዮጵያ የአዲስ ታሪክ ዘመን መክፈቻ መሆኑንነው፤ በዚህም አዲስ ዘመን ሁላችን መፈጸም ያለብን አዲስ ሥራ ይጀመራል . . . »

ቀ. ኃ. ሥ.

ይህ ጋዜጣ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ተመልሰው ከዋና መናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ በገቡ ጊዜ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ንግግር ሲያደርጉ « ይህ ቀን ላዲሲቱ ኢትዮጵያ ያዲስ ዘመን መክፈቻ ነው » ብለው የተናገሩት በመሠረት አዲስ ዘመን ተብሎ ተሰየመ ፡

«መላው ሕዝብ ወንዱም ሴቱም በለው አቅሙና መሣሪያው ለኛ ሲል ወንበዴዎቹን ለመደምሰስ ላደረገው ተጋድሎ ምንም ብናደርግ ውለታው የሚከፈል አይደለም »

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከወዳጅ አገር ጉብኝት ተመልሰው አዲስ አበባ በገቡበት ዕለት ከተወዳጅ ሕዝባቸው የተደረገ

የናፍቆት አቀባበል

ዋሰልኝ አየለ

ከታሪክ መጻሕፍት ጀርባ ማጣቀሻ ሆኖ እናገኘዋለን። የታላላቅ ሰዎች ግለ ታሪክ ሲጻፍ ምንጭ ሆኖ ይገኛል። የታላላቅ ደራሲዎችና ፖለቲከኞች ሥራዎች ይገኙበታል። አንድ ምዕተ ዓመት የተጠጉ ሁነቶች ተሰንደው ይገኙበታል። ከ80 ዓመታት በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጥበባዊ ሁኔታዎች ይገኙበታል። አዲስ ዘመን ጋዜጣ!

እነሆ ዛሬ የታሪክ ነጋሪውን ታሪክ ልንዘክር ነው። ‹‹ሳምንቱ በታሪክ›› በሚለው ዓምድ ሥር ከብዙ ዓመታት በፊት በሳምንት ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶችን እናስታውሳለን። ይህን የምናደርገው ታዲያ እንደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ያሉ አንጋፋ ታሪክ ሰናጆች ባስቀመጡት ሰነድ ነው። የሌሎችን ክስተቶች ታሪክ ሲናገር የኖረው አዲስ ዘመን ጋዜጣ እስኪ የራሱንም ታሪክ እንዘክርለት።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ እነሆ 81 ዓመታትን ተጓዘ። ባለፈው ማክሰኞ ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም 81ኛ ዓመት ሆነው። አዲስ ዘመን ጋዜጣ በዕለተ ቅዳሜ ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተመሰረተ። እነሆ ለ81 ዓመታት የአገሪቱ ብቸኛ ዕለታዊ ጋዜጣ በመሆን የአራት ሥርዓተ መንግስታትን (የአሁኑን ጨምሮ) ምንነት ሰንዶ አስቀምጧል፤ እያስቀመጠ ነው። የእነዚህ መንግስታት ባህሪም የሚታወቀው በዚሁ ጋዜጣ ነው።

አሁን ላይ ያለ ወጣት ንጉሣዊ ሥርዓቱ ምን አይነት እንደነበር አያውቅም። ቤተ መጻሕፍት በመግባት ግን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማግኘት ይችላል። የጋዜጣ ሰነድነት ከመጻሕፍትና ከሌሎች ሰነዶች ይለያል። ምክንያቱም ዜናዎች አሉበት። ዜና በወቅቱ ዜና ይሁን እንጂ ከዘመናት በኋላ ግን ታሪክ ይሆናል። ምክንያቱም የመንግስታት ዕለታዊ ክንውኖች ስለሚጻፉበት ነው።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ስሙ ከታላላቅ ደራሲዎች ጋር ይነሳል። የእነዚህ ደራሲዎች ስም ሲነሳ አዲስ ዘመን፤ የአዲስ ዘመን ስም ሲነሳ የእነዚህ ደራሲዎች ስም ተያይዞ ይጠራል። በተለይ የበዓሉ ግርማ እና የጳውሎስ ኞኞ ግን ይደጋገማል። ምክንያቱም እነዚህ ደራሲዎች በታሪክ እና በፖለቲክ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ስለፈጠሩ ነው። ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ዘሪሁን እና ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሔር አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሰሩ ታላላቅ ደራሲዎች ናቸው። ብርሃኑ ዘሪሁን የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ነበር። ሌሎች አንጋፋና ወጣት ደራሲዎችም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቋሚ ተቀጣሪነትም በፍሪላንሰርነትም፣ በውጭ ፀሐፊነትም የሰሩ ብዙ ናቸው። እነ ማዕረጉ በዛብህ፣ ደራሲ ዘነበ ወላ፣ አንተነህ ይግዛው.... ይጠቀሳሉ። እስኪ የጥቂቱን ታላላቅ ደራሲዎች እና የአዲስ ዘመን ጋዜጣን የታሪክ፣ የጋዜጠኝነትና ስነ ጽሑፍ ትዝታዎች እናስታውስ።

**በዓሉ ግርማ**

በዓሉ ግርማ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረ እና የስነ ጽሑፍ አርበኛ ነው። በዓሉ ግርማ በተለይም «ኦሮማይ» በተሰኘው መጽሐፉ ጋዜጠኝነትንም ስነ ጽሑፍንም አሳይቷል።

መጽሐፉ ጋዜጠኝነትንና ስነ ጽሑፍን የያዘ ነው። እንደ ጋዜጠኛ ያየውንና የሰማውን ጽፏል። የጋዜጠኛን ድፍረት አሳይቷል። ጋዜጠኛ አድርባይ፣ ወላዋይና ፈሪ መሆን እንደሌለበት አሳይቷል። የጋዜጠኝነት ሙያ ህይወትን እስከማጣት መስዋዕትነት የሚከፈልበት መሆኑን በተግባር አሳይቷል።

እንደ ስነ ጽሑፍ ካየነውም፣ እነሆ መማሪያ እስከመሆን ደርሷል። ለብዙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥናትና ምርምር ምንጭ ሆኗል። በጋዜጠኝነት ትምህርት ቤትም በስነ ጽሑፍ ትምህርት ቤትም ማነፃፀሪያ ተደርጓል። የስነ ጽሑፍ አላባውያን ለሚባሉት መሰረት ሆኗል። በየስነ ጽሑፍ ውይይቱ የበዓሉ መጽሐፎች ስም ይነሳል። አገላለጾቹ ስነ ጽሑፋዊ ውበት ያላቸው ናቸው። ረቂቅ አገላለጽ ይጠቀማል። ተምሳሌታዊ ትርጓሜን አሳይቷል። ፍቅርን አሳይቷል።

ለህይወቱ መጥፋት ምክንያት ስለሆነ እና ፖለቲካዊ ይዘት ስለሆነ «ኦሮማይ» ተደጋገመ እንጂ ሌሎች መጽሐፎቹም አሉት። «የቀይ ኮከብ ጥሪ የሚለው መጽሐፉም እንዲሁ ፖለቲካና ስነ ጽሑፍን የያዘ ነው። ከአድማስ ባሻገር በብዛት የሚደጋገመው በስነ ጽሑፍ ሰዎች ዘንድ ነው። ሀዲስ፣ ደራሲው እና የህሊና ደወል የሚሉትም ቢሆን ተደጋግመው የተነበቡ ናቸው። በአጠቃላይ በዓሉ ግርማ ለስነ ጽሑፍና ለጋዜጠኝነት ሙያ መስዋዕት የሆነ ሰው ነው። እንደ ታሪክ ደግሞ በወቅቱ የነበረውን ክስተት አሳይቷል።

**ጳውሎስ ኞኞ**

ጋዜጠኛ የሆኑም ያልሆኑም ሰዎች ስለ ጳውሎስ ኞኞ እና አዲስ ዘመን ጋዜጣ አንድ ነገር ያውቃሉ። ይሄውም «አንድ ጥያቄ አለኝ» የሚለው የጳውሎስ ኞኞ ጽሑፍ ነው። የትም ቦታ የጳውሎስ ኞኞ ስም ከተነሳ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የነበረው ይሄ ዓምዱ ይጠቀሳል። ጳውሎስን ለማስታወስ ሲባልም የሬዲዮ ፕሮግራም እና የህትመት ዓምዶችም ወጣ ገባ እያሉ ተሰይመዋል። በኩረጃ ሳይሆን እሱን ለማስታወስ መሆኑን እየጠቀሱ ማለት ነው።

ስለጳውሎስ ኞኞ የጋዜጠኝነት ፍቅር አንድ ጓደኛው የነበረ ሰው በሬዲዮ ሲናገር የሰማሁትን ገጠመኝ ላካፍላችሁ።

ጳውሎስ ታሞ ተኝቶ ነው። ጓደኞቹ ሊጠይቁት ከቤቱ ይሄዳሉ። ሲሄዱ በፀና ታሞ ተኝቷል። ብዙም አያናግራቸውም፤ በህመም ላይ አናጨናንቀውም ብለው ዝም ብለዋል። በቤቱ ውስጥ የተከፈተው ሬዲዮ እያወራ ነው። ጋዜጠኛው አንድ ስህተት ይሳሳታል። ይህኔ ጳውሎስ «አይ! አዳምጡትማ ይሄን ጋዜጠኛ...» ብሎ የጋዜጠኛውን ስህተት አስተካክሎ ነገራቸው። በህመም ላይ ያለ ሰው፣ እንኳን ስህተትን ነቅሶ ማውጣት ስለምን እየተወራ እንደሆነ ራሱ ልብ አይልም ነበር። ጳውሎስ ኞኞ ግን በህመም ውስጥ ሆኖ እንኳን መረጃን እያጣራ ይሰማ ነበር ማለት ነው።

ስለ ጳውሎስ ኞኞ የሚነገር ሌላ አንድ አስቂኝ ገጠመኝ ደግሞ አለ። ለስቴዲየም መስሪያ ተብሎ መዋጮ እየተዋጣ ነው። የኳስ ነገር ያልጣመው ጳውሎስ «ኧረ ይሄ ነገር ይቅር» ይላል። በጣም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ሲነግሩት «ሎሬ አንድ ጅሎች አንድ ቅሪላ ሲከታተሉ ለማየት አላዋጣም» ብሎ የተሰበሰበው ብር ለሆስፒታል ግንባታ መዋል እንዳለበት ተናግሯል።

ጳውሎስ ኞኞን የሚያውቀው ሁሉ አንድ የሚያውቀው ታሪኩ ደግሞ በመደበኛው ትምህርት ከ4ኛ ክፍል በላይ ያልተማረ ምሁር መሆኑ ነው። የታሪክ ተመራማሪ ነው። ኢ-መደበኛ ትምህርት እና በጥልቅ ንባብ ምሁር መሆን እንደሚቻል ያሳየ ሰው ነው። «የሴቶች አምባ፣ አጤ ምኒልክ ፣ አጤ ቴዎድሮስ ፣ አስደናቂ ታሪኮች ፣ የኢትዮጵያና የጣሊያን ጦርነት ፣ አራዳው ታደሰ ፣ የኔዎቹ ገረዶች ፣ የጌታቸው ሚስቶች ፣ ምስቅልቅል፣ እንቆቅልሽ ፣ አጤ ምኒልክ ከውጭ ሀገራት የተፃፃፏቸው ደብዳቤዎች፣ አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተፃፃፏቸው ደብዳቤዎች» የጳውሎስ ኞኞ መጽሐፎች ናቸው። ይሄ ሰው ጋዜጠኛ፣ ደራሲ፣ የታሪክ ተመራማሪ ብቻ አልነበረም። በእርሻ ሚኒስቴር (ለዚያውም ገና በ17 ዓመቱ) የእንስሳት ሐኪም ሆኖም ሰርቷል።

ጳውሎስ በጋዜጠኝነት ዘርፍ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ፣ በኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንዲሁም በኢትዮጵያ ራዲዮ ለአመታት መረጃ በመስጠት፣ በማስተማርና በማዝናናት ህዝብን በማንቃት በጋዜጠኝነት ሙያው አንቱታን አትርፏል።

ባለፈው ማክሰኞ ግንቦት 30 ቀን የአዲስ ዘመን ጋዜጣን 81ኛ ዓመት ነበር። የሚገርመው ኢጋጣሚ ጳውሎስ ኞኞ ደግሞ ህይወቱ ያለፈው በዋዜማው ግንቦት 29 ቀን 1984 ዓ.ም ነው። ከአዲስ ዘመን ጋር ያላቸውን ቁርኝት ታሪክም አቀራርቦታል። እነሆ መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይውልና ሲወደስ ይኖራል።

**ብርሃኑ ዘሪሁን**

ዕውቁ የስነ ጽሑፍና የታሪክ ሰው ብርሃኑ ዘሪሁን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበር። የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ እያለ ከመንግስት ጋር ይጋፈጥ እንደነበርም ይነገራል።

ብርሃኑ ዘሪሁን በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ውስጥ ትልቅ አሻራ አስቀምጧል። ለታሪካዊ ልቦለድ አጻጻፍ ፈር ቀዳጅ ሆኗል። የተውኔት ሥራዎችን እና የታሪክ ምርምሮችን ሰርቷል።

«የቴዎድሮስ እንባ፣ የታንጉት ምስጢር፣ ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ፣ ማዕበል የአብዮት ማግስት፣ ጨረቃ ስትወጣ»፣ አማኑኤል ደርሶ መልስ፣ የእንባ ደብዳቤዎች፣ የበደል ፍፃሜ» የሚሉት መጽሐፍት ሲሆኑ፣ ‹ባልቻ አባነፍሶ፣ ‹‹ጣጠኛው ተዋናይ፣ የለውጥ አርበኞች፣ ሞረሽ...» የተሰኙ ተውኔቶችን ጽፏል።

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ ሲነሳ የእነዚህ ሁሉ ሰዎች ታሪክ ነው የሚነሳው። ለዚያውም ትልልቅ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሳይዳሰሱ ማለት ነው። በግለሰብ ደረጃ እንኳን የአዲስ ዘመን ጋዜጣን ስም የሚያስጠሩ ብዙ ታላላቅ ሰዎች አሉ።

በፖለቲካው ዘርፍ ደግሞ ንጉሣዊ ሥርዓቱ ምን እንደነበር፣ በወቅቱ ምን አይነት ዜናዎች ይሰሩ እንደነበር፣ ምን አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ይደረጉ እንደነበር ይነገርናል። በወታደራዊው የደርግ መንግሥትም ሆነ በአብዮታዊው ኢህአዴግ ዘመን የነበሩ ሁነቶችን ሁሉ ከዚሁ ጋዜጣ ላይ ማግኘት ይቻላል። እነሆ በአሁኑ የብልጽግና አስተዳደርም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዕለታዊ ሁነቶችን እየዘገበ ዛሬን ለነገ እያስቀመጠ ነው።

ጋዜጣው «አዲስ ዘመን» የሚለውን ስያሜ እንዴት አገኘ? የሚለውን እና የመጀመሪያው ዕትም ላይ የወጡ ጽሑፎችን እናስታውሳችሁ።

ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከስደት ከቆዩበት እንግሊዝ ተመልሰው አዲስ አበባ ሲገቡ ለሕዝቡ ባደረጉት ንግግር «... ከማናቸውም አስቀድሞ ለሁላችሁም ልነግራችሁና ልትረዱት የምፈልገው ይህ ቀን ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የአዲስ ዘመን መክፈቻ መሆኑን ነው። በዚህም በአዲስ ዘመን ሁላችን መፈፀም ያለብን አዲስ ስራ ይጀምራል ...» ብለው ስለነበር ጋዜጣውም «አዲስ ዘመን» ተብሎ ተሰየመ።

በጋዜጣው የመጀመሪያ ዕትም የመጀመሪያ ገጽ ላይ ንጉሰ ነገሥቱ በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ከአምስት ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላ አዲስ አበባ ሲገቡ የሚያሳየውን ፎቶግራፍ እና ስለጋዜጣው ዓላማ የሚገልፅ ጽሑፍ ወጥቶ ነበር።

« ... ይህ አዲስ ዘመን ተብሎ የተሰየመው ጋዜጣ ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ለመላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የረዳትነቱን ስራ ይሰራ ዘንድ ተመሰረተ። ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ለኢትዮጵያ አዲስ በሆነው ዘመን ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚያስፈልገውን ስራ ሁሉ እያመለከተ፣ ይልቁንም ሕዝብ ለአገሩ፣ ለመሪውና ለንጉስ ነገሥቱና ለንጉስ ነገሥቱም መንግሥት ማድረግ የሚገባውን እየገለፀ የበጎን ስራ መንገድ የሚመራ እንዲሆንም ይህ ጋዜጣ በግርማዊ ንጉስ ነገሥት ተመሰረተ።

ስራውም በሦስት ቃሎች ይጠቃለላል። እውነት፣ ረዳትነትና አገልግሎት። እውነት ስንል በዚህ ጋዜጣ የሚነገረው ነገር ሁሉ መሰረቱ በፍጹም እውነትን እየተከተለ ለአንድ ጥቅም ብቻ ያልሆነና ለመላው ጥቅም የሚሰራ እንዲሆን ነው። አገልግሎት ስንል የኢትዮጵያን ነፃነት ለመመለስ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው የራሳቸውን ጥቅም ሁሉ አስወግደው ለሕዝባቸውና ለአገራቸው ሲሉ የሰው አቅም ሊሸከመው የማቻለውን ድካም ተቀብለው ማንኛውም ሰው ሊያደርገው ያልተቻለውን በኢትዮጵያ ሕይወት ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ያልታየውን ስራ ከፍፃሜ ላደረሱ ለተወደዱ ንጉሰ ነገሥታችንና ላቆሙት መንግሥት የሚያገለግል እንዲሆን ነው...» የሚል ነበር።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ከእድሜው ቀድሞ የበሰለው ተሸላሚ

አቤል ገ/ኪዳን

በቅርቡ የጉማ ሽልማት ተካሂዶ ነበር። ሽልማቱ በተለይ በፊልሙ ዘርፍ በ2013 ጥሩ ስራዎችን ያቀረቡ የጥበብ ሰዎች የተሸለሙበት እና በማህበራዊ ሚዲያም የብዙዎች መወያያ የነበረ ፕሮግራም ነበር። በዚህ የሽልማት መርሀ ግብር ላይ ወርቃማውን ዋንጫ ይዘው ወደቤታቸው ከሄዱ የጥበብ ሰዎች መሀከል አንዱ የዛሬው እንግዳችን ነው። በጉማ አዋርድ ላይ ማን ያዘዋል በሚለው ፊልሙ በ11 ዘርፎች ታጭቶ በሶስቱ ዋንጫውን የወሰደው እና ከሶስቱ ሽልማቶቹ መሀከል ደግሞ ሁለቱ የግሉ የሆኑለት በዚህም የተነሳ የ2013 የአመቱ ምርጥ ደራሲ እና ዳይሬክተር የተሰኘው ወጣቱ ጥበበኛ ኑር አክመል ዛሬ አብሮን ይቆያል።

የተወለደው እዚሁ አዲስ አበባ በተለምዶ አስኮ ጨረታ በሚባለው አካባቢ ነው። ቀኑ ጳጉሜ 3 አመቱም 1989 ኢ.ም ነው። አሁን 25ኛ አመቱ ላይ ነው ማለት ነው። አባቱ አቶ አክመል ሰማን እና እናቱ ወ/ሮ ብርሀኔ ተፈሪ አራት ልጆች ያሏቸው ሲሆን ከነዚህ 4 ልጆች ኑር የመጨረሻው ነው። የአቶ አከመል ቤተሰብ ለየት ያለ ነው። ኑር የቤተሰቡን ታሪክ "ፊልም ይወጣዋል" ይላል። ምናልባትም ስልጡን እና ዴሞክራሲያዊ ቤተሰብ ነው ልንለው እንችላለን። ከአራቱ ልጆች ኑር እና ወንድሙ ሙስሊም ሲሆኑ ሁለቱ ሴቶች ደግሞ ኦርቶዶክስ ናቸው። በቴዲ አፍሮ ሙዚቃ እንደተባለው አንቺም በሀይማኖትሽ እኔም በሀይማኖቴ ፤ መኖር እንችላለን አይጠበንም ቤቴ የተባለበት ሁሉም ተዋድዶ እና ተስማምቶ የሚኖርበት ቤት ነው የአቶ አክመል ቤት።

ኑር እድሜው ለትምህርት ሲደርስ መጀመሪያ የገባው እዚያው ቤታቸው አቅራቢያ የሚገኘው ቃሌ አጸደ ህጻናት ነበር። ከዚያም ከአንድ እስከ ስምንት ጉለሌ ፋና አንደኛ ደራጃ ሲማር ሁለተኛ ደረጃውን ደግሞ አስኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቀቀ። የመሰናዶ ትምህርቱን ደግሞ መድህኔአለም ሁለተኛ ደረጃ ተማረ።

ኑር በተማሪነት ዘመኑ እንደ ብዙሀኑ ተማሪ ለትምህርት የተለየ ፍቅር የሌለው እና እንዲሁ ሲጫወት እና ወዲያ ወዲህ ሲል ቢውል የሚወድ ልጅ ነበር። ሙሉ ትኩረቱን ትምህርት ላይ አለማድረጉ ግን ወደ ኪነ ጥበብ አልመራውም። እንዲያውም የሱ ልብ ያለው ስፖርት ላይ ነበር። ቀንደኛ የማንችስተር ዩናይትድ ደጋፊ ነው። ስለዚህም እሱም ሆነ ቤተሰቦቹ ምናልባት ወደፊት ጋዜጠኝነትን ተምሮ የስፖርት ጋዜጠኛ ይሆናል እንጂ ወደ ጥበብ የሚወስደው መንገድ ይኖራል ብለው አላሰቡም። ህይወት ግን ለኑር ሌላ የራሷ የሆነ መንገድ ቀይሳ እየጠበቀችው ነበር።

በየጊዜው ከክፍለ ሀገር ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ በጻጋው የሚባል የነ ኑር ዘመድ አለ። ሲመጣ ኑርን ሲኒማ ይዞት ይገባል። ያኔ ኑር የመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበር። ወቅቱ ደግሞ እነ ረቡኒ እና መሰል ምርጥ ፊልሞች በሲኒማ ቤቶች የሚታዩበት ወቅት ነበር። ኑር እነዚያን ፊልሞች ሲያይ ከመዝናናት በላይ ፊልም የመስራትን ምኞት ፈጠሩበት። ከዚያ ደግሞ አንድ ቀን ወንድሙ የሚራክል የፊልም ትምህርት ቤትን ማስታወቂያ በራሪ ወረቅት ይዞ ቤት መጣ። ኑር ለመማር ወሰነ። በወቅቱ የመሰናዶ ትምህርቱን ጨርሶ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ አካውንቲንግ ተማሪ እንዲሆን ተመድቦ የነበረ ቢሆንም እሱ ግን እዚሁ አዲስ አበባ ለመማር ነው የወሰነው። እናም የፊልም ትምህርት ቤቱ ገብቶ ተማሪ ሆነ። አንጋፋው የጥበብ ሰው የክብር ዶክተር ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) የሚያስተምሩበት በተለምዶው ፋዘር ቤት የሚባለው ትምህርት ቤትም ተቀላቀለ። እዚያ ብዙ እሱን የሚመስሉ እና ከሱም የሚበልጡ የጥበብ ሰዎችን አገኘ። ከዚያም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማታው ክፍለ ጊዜ የቴአትሪካል አርት ተማሪ ሆኖ ተመዘገበ። በወቅቱ የጋዜጠኝነት ተማሪ ይሆናል ብለው አስበው የነበሩት እናቱ በውሳኔው ቢደናገጡም ነገር ግን የልጃቸውን መሻት እሳቸውም ሆነ ጋሽ አክመል ሊገቱት አልፈለጉም። "መጀመሪያ ራሱ ያሰኘውን ይሞክርና በኋላ እንሞክርበታለን ብለው ነው መሰለኝ እድል ሰጥተውኛል" ይላል።

ትምህርቱ ተጀመረ። ኑር ትምህርቱን እየተማረ ረፍት አልነበረውም። የተማረውን በተግባርም ይሞክር ነበር። ስክሪፕቶችን ይጽፋል ፤ ባለሙያዎች እንዲያዩለትም ይሰጣል። በእጅ የተጻፈ እሷ ናት የተሰኘ 120 ገጽ ስክሪፕት በእጁ ጽፎ ነበር። ሌሎችም ተጨማሪ ሁለት ሶስት




ኑር አክመል

ስክሪፕቶችን ጽፏል። ከዚያ የመጀመሪያ ስራው የሆነውን አቶ እና ወይዘሮ ጻፈ። እንዲያዩትም ለአንጋፋዎቹ ሰለሞን ሙሄ እና ቃልኪዳን ጥበቡ ሰጣቸው። ያኔ ገና የ20 አመት ጎረምሳ ነበር። ልጅ ነው ብለው ሳይንቁ ስክሪፕቱን አዩ ፤ አደነቁለትም። ወደ ስራ ተገባ። ባለሙያ ተመረጠ ፤ ዝግጅቶችም ተጠናቀቁ። የቀረው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ፡ ገንዘብ። ሊያውም 150ሺ ብር።

ቤት ሄደ። ፊልም ስለማየት እንጂ ፊልም ስለመስራት ምንም ግንዛቤው ለሌላቸው ቤተሰቦቹ ሀሳቡን አስረዳ። ብዙም ስላልገባቸው ባይቃወሙትም ገንዘብ ለመስጠት ግን አልደፈሩም። ስለዚህም አዲስ እና ለየት ያለ የቅስቀሳ ዘዴ ይዞ መጣ። ዝናብ ሲዘንብ የጣሪያው ፍሳሽ ተሰብስቦ የሚወርድበት አሸንዳ ስር ሄዶ ተቀመጠ። ይህን ያየችው አንደኛዋ እህቱ ጥያቄው ምን ያህል ጽኑ እንደሆነ ስታውቅ ለክፉ ቀን ብላ ያስቀመጠችውን ወደ 70ሺ ብር ገደማ ልትሰጠው ወሰነች። ወትሮም ቢሆን ልቧ የማይጨክነው እናት ወ/ሮ ብርሀኔም ለቁርጥ ቀን ይሆናል ብላ ያስቀመጠችውን ብር አውጥታ ልትሰጥ ወሰነች። ብሩ ተገኘ። ፊልሙም ተሰራ። የምርቃቱ ቀን ቤተሰቦቹ ሁሉ እንዲያውም ምን ጉድ ሰርቶ ይሆን ብለው ነበር የተገኙት። ፊልሙ ታየ። ህዝብ ወደደው። ተነስቶ አጨበጨበለት። እናትና እህት ገንዘባቸውን ውሀ እንዳልበላው አዩ። ከሁሉ በላይ ግን የጋሽ አክመል ቤተሰብ ልጃቸው ፊልም ውስጥ እንዲገባ መፍቀዳቸው ስህተት እንዳልነበር አዩ።

በመጀመሪያ ፊልሙ ስኬት የተነቃቃው ኑር ሁለተኛ ፊልም ሊሰራ ተነሳ። ባለቤት የሚል ፊልምም ሰራ። አንጋፋው ፈለቀ የማርውሀ ነበር ተዋናዩ። ስኬታማ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ሆነው ነበር የጀመሩት። ነገር ግን ፊልሙ እንደታሰበው በህዝብ ዘንድ አልተወደደም። እሱና አብሮት የሰራው ወዳጁ የግማሽ ሚሊየን ብር ኪሳራ ተከናንበው ቁጭ አሉ። በወቅቱ የነበውን ስሜት ሲያስታውስ "ለወር ገደማ ከቤት አልወጣሁም" ይላል ኑር። ፊልሙ በወቅቱ በሲኒማ ቤት ተመልካቾች ተወዳጅነት አያግኝ እንጂ በኋላ ላይ ግን ተወዳጅ እንደሆነ እና ብዙ ገንቢ አስተያየቶችም እንደመጡ በተለይም ፊልሙ ከትዳር ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብዙ ባለትዳሮች ትምህርት እንደቀሰሙበት እንደነገሯቸው ኑር ይናገራል።

ቀጠለ። ካደረበት ጉዳት ለማገገም መፍትሄ ያስፈልጋል። መፍትሄው ደግሞ ሌላ ፊልም መስራት ነው። ኮሜዲ ፊልም ለመስራት ተነሳ። ስቁ ልሙት የሚል ኮሜዲ ፊልም ሰራ። ይሄኛው ደግሞ ተወደደለት። እንደገና አገገመ። ወደ መስመሩ ተመለሰ። ቀጣዩ ፊልም ታሰበ። አንድ ቀን ቡና እየጠጡ ጓደኛው የነገረውን ታሪክ ፊልም ሊያረግ ወሰነ። ማን ያዘዋል የሚል ፊልም ተሰራ። ፊልሙ ተሰርቶ ፤ ማስታወቂያ ለህዝብ ተነግሮ ለህዝብ ሊቀርብ ሲል ግን ያልታሰበ ችግር መጣ። ኮሮና ገባና ሲኒማ ቤቶች ተዘጉ። ምንም ማድረግ ስለማይቻል ኑር እና ጓደኞቹ እጃቸውን አጣጥፈው ቁጭ አሉ። ያኔ ለማንበቢያ እና ለማሰቢያ ጊዜ አገኘ። ከዚያም ወደ ክሊፕ እና ማስታወቂያ ስራዎችም ገባ። በወቅቱ ከሰራቸው የሙዚቃ ክሊፖች መሀከል የመሳይ ተፈራ ደሞ ደሞ ፤ የሀሌሉያ ካንተ ጋራ ፤የኩኩ ሰብስቤ ድማማ ፤የ ህብስት ጥሩ ነህ ቀረ እንዴ ተጠቃሽ ናቸው። ከዚያ ኮሮናው ጋብ ሲል እና ሲኒማ ቤቶች ሲከፈቱ ፊልሙ ለእይታ በቃ። እነሆ ከሳምንታት በፊትም የአመቱ ምርጥ የፊልም ሰውም ተባለበት።

በአሁኑ ወቅት ለሌላ ፊልም ዝግጅት ላይ ያለው ኑር በዲኤስ ቲ ቪ ሁለት ጉልቻ የተሰኘ ከደቡብ አፍሪካው አንሜሪድ የተሰኘ ፊልም የተቀዳ ተከታታይ ድራማ እያዘጋጀም ይገኛል። ስለ ሽልማቱ ሲያስብ በብዙ ታላላቅ እና ለሲኒማው ዘርፍ ማደግ ብዙ መስዋእትነት የከፈሉ ሰዎች ፊት ሽልማት መቀበሉ ትልቅ ኩራት እንደፈጠረለት ይናገራል። ኑር የፊልም ዘርፉ እንዲያድግ ዲሲፕሊን እና ጠንካራ ስራ ያስፈልገናል ይላል። "ጠዋት ዝም ብላ ከቤት የወጣች ልጅ ከሰአት ቤቷ ስትመለስ ተዋናይ ሆና ከመጣች ጥሩ አይደለም። ሀገራችን ብዙ ህዝብ አላት ፤ ከዚህም መሀከል ብዙሀኑ ወጣት ነው። ይህ የሚፈጥረው ብዙ እድል አለ። ናይጄሪያን ፤ ህንድን ማየት ትችላለህ። አሁን ወደ እኛም እየመጡ ያሉ አዳዲስ ትልልቅ እድሎችም አሉ። እነሱን ለመጠቀም ካስፈለገ ደግሞ በዚያ ልክ ራሳችንን ማዘጋጀት አለብን" ይላል። ከዚህም ባለፈ ኑር "ፊልም ለማየት አንድ ሰው ወደ ሲኒማ ሲመጣ ሊከፍል የሚገባው 5 ብር ብቻ ነው ብዬ አምናለሁ ይላል። የሚያስፈልገው ከአንድ ሰው ለአንድ ፊልም መቶ ብር መቀበል ሳይሆን ፊልሙ ለተመልካች ተደራሽ የሚሆንበትን እድል ማስፋት ነው ብዬ አምናለሁ" ይላል።

ኑር ኳስ ይወዳል። ስራውም መዝናኛውም ፊልም ቢሆንም እንኳ ከዚያ ውጭ ያለውን ጊዜ የሚያሳልፈው እግር ኳስ በማየት እንደሆነም ይናገራል። በመጨረሻ በዚህ በጉርምስናው ወራት ለስኬት እንዲበቃ ላገዙት ሰዎች ምስጋናውን እንዲቀርብ እድል ሰጠነው። "በመጀመሪያ እዚህ ቦታ ላይ እንድደርስ በሁሉም መንገድ ላገዙኝ ቤተሰቦቼ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፤ በመቀጠል በስራዬ ለሚያግዙኝ የነፍስ ሰዎቼ የስራ ባልደረቦቼ ምስጋና አቀርባለሁ። በመጨረሻም ይህ ሙያ እዚህ እንዲደርስ መስዋእትነት ለከፈሉ ሰዎች ምስጋናዬን አቀርባለሁ" ብሏል።

**ኑር በተማሪነት ዘመኑ እንደ ብዙሀኑ ተማሪ ለትምህርት የተለየ ፍቅር የሌለው እና እንዲሁ ሲጫወት እና ወዲያ ወዲህ ሲል ቢውል የሚወድ ልጅ ነበር። ሙሉ ትኩረቱን ትምህርት ላይ አለማድረጉ ግን ወደ ኪነ ጥበብ አልመራውም**




# ናትናኤልና የህልም ግብግቡ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ልጆች እንደምን ሰነበታችሁ፤ ደህና ናችሁ አይደል? ሳምንቱን እንዴት አሳለፋችሁት ? በጥናት እንደምትሉኝ እተማመናለሁ። በተለይ ደከም ያላችሁበት የትምህርት አይነት ላይ ለየት ያለ ትኩረት አድርጋችሁ እንደምታነቡ አስባለሁ። ምክንያቱም ለቀጣዩ ውጤታችሁ የተሳካ መሆን ግድ ይህንን ማድረግ ስላለባችሁ። ስለዚህም በደንብ በማጥናት ጥሩ ውጤት ለማምጣት ስሩ እሺ።

ልጆች ዛሬም እንደተለመደው ጎበዝና በሳይንሱ ዘርፍ የተሻለ ነገር ይዞ ለመምጣት የሚጣጣር ተማሪ ይዤላችሁ ቀርቤያለሁ። ልጁ ናትናኤል ዮሐንስ ይባላል። ተወልዶ ያደገው በአዲስ አበባ ሲሆን፤ የዳግማዊ ምኒልክ አጸደ ሕጻናትና መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ሳይንስ ላይ ልዩ ፍላጎት ያደረበት ተማሪ ነው።

ትምህርቱን የሚማረው ከአያቱ ጋር ሆኖ ነው። በዚህም የአያት ልጅ ቅምጥል እንደሚባለው አይነት የልጅነት ጊዜን ያሳልፋል። በዚያ ላይ አያቱ ባይማሩም የሚያስተምሩትና ያስለመዱት ብዙ ነገር አለ። ከእነዚህ መካከል ሰዎችን መርዳት አንዱ ነው። ‹‹መስጠት ለሰዎች ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለራስም ፍቅርን መቀበልም ነው›› የሚል እምነት ያለው ልጅ እንዲሆን አድርጎታል። እምነቱን ደግሞ በተግባር የሚተረጉም ነው። ለምሳሌ በትምህርት ቤት ብቻ ብዙ ነገር ያደርጋል።

አንዱ በምገባ ወቅት ለህጻናቱ የሚያደርገው እንክብካቤ ሲሆን፤ ብዙ ጊዜ ሲሯሯጡ ይደፋባቸዋልና ዳግም ለመጠየቅ ስለሚፈሩ ሳህኑን ሰጥተው ለመውጣት ይገደዳሉ። በዚህ ጊዜ ከእነርሱ እኔ ረሃብን መቋቋም እችላለሁ ብሎ ያስባልና የእርሱን ምሳ ሰጥቷቸው ይወጣል። ደስ የሚል ባህሪ ነው አይደል ልጆች? አያችሁ አንዱ ለአንዱ መኖር እንዲህ ነው። እናንተም ይህንን መልካምነት መገለጫችሁ አድርጉ እሺ።

ናትናኤል በልጅነቱ ነገሮችን ፈታቶ ማየት የሚወድ ሲሆን፤ ውስጣዊ ነገሮች በጣሙን ያጓጉቷል። በተለይ ኤሌክትሮኒክስ ነገሮች እጅግ ከሚስቡትና ከሚፈታታቸው መካከል ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ ውስጡን ካየ በኋላ በትኩረት ስለሚፈታታቸው ምንም አይነት ስህተት ሳይፈጽም ወደነበሩበት ይመልሳቸዋል። ይህ ስሜቱ ደግሞ ሳይንቲስት እንዲሆን ያስመኘዋል። በተጨማሪም ሜካኒካል ሳይንቲስት መሆን እጅግ የሚማርከው ነገር ነው።

ተማሪ ናትናኤል በመልካም ርምጃችን አጸደ ሕጻናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማር ፍላጎቱን መሰረት ያደረጉ በርካታ ነገሮችን ሠርቷል። እነዚህ ሥራዎቹ ደግሞ የተለያዩ ብቻ ሳይሆኑ ትምህርት ቤቱን ያስጠሩም ናቸው። ናትናኤል እንደሚለው፤ ጊዜው ቅርጻቅርጽ መሥራት ላይ ጥሩ አቅም እንደነበረው ያየበት ነው። ምክንያቱም በወረቀት ጭቃ አቡክቶ በጣም ትልቅ አዞ ሠርቷል። በተጨማሪም ለልጆች መማሪያ የሚሆኑ ከእንጨት የተሰሩ ቅርጻቅርጾችንም ሰርቶ አበርክቷል።

‹‹አሁን ላይ ያላጠጣነው አበባ አያድግም። ከአሁኑ ስንንከባከበው ነው ጥላ የሚሆነን›› የሚለው ተማሪ ናትናኤል፤ ትምህርታችንንም ሆነ ሌሎችን ማገዙ በጊዜው መሆን እንዳለበት ያስረዳል። እርሱም ይህንኑ ነው የሚያደርገው። ጊዜውን በምንም መልኩ ከትምህርት ውጪ ማሳለፍ አይፈልግም። ስኬቱ ላይ የሚያደርሰውን ተግባርም ከመሞከር ወደኋላ አይልም። ሁልጊዜ መሞከር ከምንም በላይ ያስደስተዋል።

በመሞከር ውስጥ አብዝቶ መውደቅ እንዳለም ያውቃልና ወደቅሁ ብሎ ተስፋ አይቆርጥም። ደጋግሞ ይሞክራል። በዚህም ብዙ አዲስ ናቸው የሚባሉ የፈጠራ ሥራዎችን ከውኗል። ከጓደኞቹ ጋር አሁንም የተለያዩ ተግባራትን እየከወነ ይገኛል። አንዱና ዋነኛው ቬንትሬተር ሲሆን፤ በተሻለ መልኩ ለመሥራት እየጣረ እንደሆነም አጫውቶናል።

ልጆች ናትናኤልና ጓደኞቹ ሙቀት በሚያስቸግርበት ወቅት ከውጪ ከምናመጣ በአገር ውስጥ አምርቶ መጠቀም ይቻላል በሚል ተግባሩን እየከወነ የሚገኙ ሲሆን፤ እጅግ የሚደንቅ ጥበብን ለመጠቀም አቅዷል። የመጀመሪያው ገመድ አልባ እንዲሆንና በብሉቱዝ እንዲሠራ ማድረግ ነው። እንደሚሳካላቸውም ያምናል።

ናትናኤል ከተማሪዎች ጋር አብሮ መሥራት የሚያስደስተው ልጅ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ የትምህርት አቀባበሉ በጣም ፈጣን እንዲሆንለት አስችሎታል። ሁልጊዜ ከጥናት በኋላ አዳዲስ ነገሮችን እንዲያይም ረድቶታል። በተለይ የጀመራቸው ሥራዎች ካሉ እነሱን ለማጠናቀቅ የማይቆፍረው ድንጋይ አይኖርም። ዩቲውብና መሰል ማህበራዊ ድረገጾችን በርብሮ መረጃ እንዲያገኝ ያግዘዋልም።

ሌላው የናትናኤል ልዩ ባህሪ ትምህርቱን የሚያጠናው ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤት ከገባ በኋላ መሆኑ ነው። ምክንያቱም ቤተሰብ ቤት ውስጥ ካለ ሀሳቡን ሰብስቦ ማንበብ አይችልም። ስለሆነም እነርሱ ሳይመጡ መጀመሪያ የቤት ሥራውን ያስቀድምና ከዚያ ወደ ጥናቱ ይገባል። ዛሬ የተማረውን ዛሬውኑ ለማጥናትም ይሞክራል። ስለዚህም ለነገ የሚለው ነገር የለውም።

ትምህርትን አብዝቶ የሚወድና ብዙ ጊዜውን ለጥናት የሚሰጥ ቢሆንም ከትምህርት ጊዜና ከጥናት ውጪ ደግሞ የተለያዩ ነገሮችን መሥራት ያስደስተዋል። አያቱን ማገዝ፤ እግር ኳስ መጫወትም ይወዳል። ከሁሉም በላይ ግን የፈጠራ ሥራዎቹን የተሻለ ለማድረግ የሚያስፈልገውን



ተግባር መከወን ይማርከዋል። እናም ጊዜው የሚያልፈው ይህንን በማድረግ እንደሆነም ነግሮናል። ልጆች እናንተም በትምህርታችሁ ውጤታማ እንድትሆኑ ጊዜያችሁን በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ። በተለይም ልዩ ትኩረታችሁ መሆን ያለበት ትምህርትና ትምህርታችሁ ብቻ መሆን ይገበዋል። ጊዜው ደግሞ ሰኔ በመሆኑ ለፈተና ልዩ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባችኋል በርትታችሁ አጥኑ። ለዛሬ ይዘንላችሁ የቀረብነው ልጅ ደግሞ ይህንን በሚገባ ያሳየ በመሆኑ ከእርሱ ተማሩ። በሚቀጥለው አምድ እስከምንገናኝ መልካም ሰንበት ይሁንላችሁ!!

# ስፖርት





# አዲስ ዘመን ጋዜጣና የአፍሪካ ዋንጫ ትዝታዎቹ

**ቦጋለ አበበ**

በ1933 ዓ.ም ተቋቁሞ በየእለቱ ለአንባቢያን የሚደርሰው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ባለፉት ሰማንያ አንድ ዓመታት በስፖርቱ ዙሪያ የተለያዩ የአገር ውስጥ ውድድሮችንና ታላላቅ ዓለምአቀፍ የስፖርት መድረኮችን በመከታተል ታሪካዊ ዘገባዎችን አስነብቧል። ከታላቁ የስፖርት መድረክ ኦሊምፒክ አንስቶ እስከ ዓለም ዋንጫና የአፍሪካ ዋንጫ እንዲሁም የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች ድረስ በርካታ አይረሴ ዘገባዎችን ለአንባቢዎቹ እንካችሁ ከማለት ባሻገር ታሪክን ሰንዶ ለአሁኑ ትውልድ ማሸጋገር ችሏል። አዲስ ዘመን ባለፈው ማክሰኞ ሰማንያ አንደኛ ዓመቱን አክብሯል።

ይህ አንጋፋ የሕትመት ሚዲያ ካለፉት ስምንት አስርት ዓመታት በላይ በተለይም ኢትዮጵያ በዓለምአቀፍ መድረኮች ኦሊምፒክንና የአፍሪካ ዋንጫን በመሳሰሉት ውድድሮች በደመቀችባቸው ዘመናት ለንባብ ያበቃቸው ታላላቅ ዘገባዎች የስፖርቱ ማህደር አንድ አካል ናቸው።ከነዚህ ታሪካዊ ዘገባዎች መካከልም በተወዳጁ የአፍሪካ ዋንጫ በተለይም ኢትዮጵያ በውድድሩ ዋንጫ ያነሳችበትና ብቸኛው ትውልድ የሚኮራበት ሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ወቅት የነበረውን ታሪካዊ ዘገባ በዛሬው የስፖርት ማህደር አምዳችን እየቀነጨብን መለስ ብለን እንመለከታለን።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ እግር ኳስ የመሰረት ድንጋይ ያኖረች አገር እንደመሆኗ መጠን የመድረኩን ጣፋጭ ድል ለአንድ ጊዜም ቢሆን መጎንጨት ችላለች። ኢትዮጵያ በወርቃማ የእግር ኳስ ዘመኗ የአፍሪካ ዋንጫን ከአምስት አስርት ዓመታት በፊት ማንሳት ስትችል አዲስ ዘመን ጋዜጣ ኢትዮጵያ አዘጋጅ አገር እንደመሆኗ መጠን ከመስተንግዶው ጀምሮ እስከ ዋንጫው ፍፃሜ ዘገባዎችን ለአንባብያን ሲያደርስ



**አዲስ ዘመን ጋዜጣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለቡድኑ አምበል ሉቺያኖ ቫሳሎ የአፍሪካ ዋንጫውን ሲያበረክቱ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ ይዞ ወጥቶ ነበር፣**

የነበረ ግንባር ቀደም የህትመት ውጤት ነበር። ጥር 6ቀን 1954 የአፍሪካ ዋንጫ አስተናጋጇ ኢትዮጵያ የመክፈቻ ጨዋታውን ከቱኒዚያ ጋር ያደረገችውን ጨዋታ እውቁ የስፖርት ጋዜጠኛ ሰለሞን ተሰማ ጥር 9ቀን 1954 ለአንባቢያን በበቃው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የስፖርት አምድ ላይ ያቀረበው ዘገባ የሚከተለውን ይመስል ነበር።

«የሦስተኛው ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫ የፉትቦል ውድድር ጥር 6ቀን 1954 ዓ.ም ከቀትር በኋላ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስታድዮም ላይ በኢትዮጵያና ቱኒዚያ ብሔራዊ ቡድን መካከል ተጀምሮ የኢትዮጵያ ቡድን 4ለ2 ማሸነፉን ከጨዋታው ስፍራ በመገኘትና በራዲዮን በመስማት ሴት ወንዱ፤ ልጆችና ሽማግሌዎች ተባብለው ሳይከፋፈሉ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከልብ የተደሰተ በመሆኑ ሰሞኑን በመስሪያ፤ በመኖሪያ፤ በሆቴልና በቡና ቤቶች፤ በገበያና ንግድ ሱቆች፤ በሴይቼንቶና በአውቶብስ ውስጥ እንዲሁም በልዩ ልዩ አደባባዮች የሚወራው ወሬ አንዳችም ጣልቃ ሳይገባበት የኢትዮጵያን ቡድን አድናቆት የተመልካችን ሁኔታና ይኸንኑ የመሳሰሉ ወሬዎች ብቻ ናቸው»።ሰለሞን የጨዋታውን መክፈቻ በእዚህ መልኩ ካተተ ከቀናት በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በተመሳሳይ ውጤት ግብፅን በፍፃሜ ጨዋታ በመርታት እስካሁን የምንጠቅሰውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ትልቅ ስኬት ማስቀረት ችሏል።

በወቅቱም አዲስ ዘመን ማክሰኞ ጥር 15 ቀን 1954 ዓ.ም ባወጣው እትሙ የፊት ገፅ ላይ « ቀልጣፋው የኢትዮጵያ ምርጥ ቡድን የግብፅን ቡድን 4ለ2 አሸነፈ» በሚል ርእስ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለቡድኑ አምበል ሉቺያኖ ቫሳሎ የአፍሪካ ዋንጫውን ሲያበረክቱ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ ይዞ ወጥቷል። የዘገባው መግቢያም የሚከተለውን ይመስላል« ለ3ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የሚደረገው የእግር ኳስ ውድድር ጥር 13 ቀን 1954 ዓም ባለፈው እሁድ ቁጥሩ ከ50ሺህ የማያንስ ህዝብ በተሰበሰበበት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስታድዮም ተደርጎ ፤ የኢትዮጵያ ምርጥ ቡድን የግብፅን ብሔራዊ ቡድን 4ለ2 አሸንፎ የአፍሪካን ዋንጫ ወስዷል። በሁለቱ አፍሪካዊ ቡድኖች መካከል የሚደረገውን ውድድር ለማየት በስታድዮሙ ውጭና ግቢ አሰፍስፎ ይጠብቅ የነበረው ተመልካች ታሪካዊ አቀባበል የሚመሳሰል ነበር። ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት ግርማዊ ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግሥት ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማችን፤ አስፋ ወሰንን፤ ልዑል ራስ እምሩንና ሌሎችንም የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው በፖሊስ ሰራዊት ሞተር ብስክሌተኞች ታጅበው ከስታድዮም ደረሱ»።

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ከፍተኛ ንቅናቄን በፈጠረው የ2013 የደቡብ አፍሪካ ዋንጫም አዲስ ዘመን ከዘመኑ ጋር ተጉዞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከሰላሳ አንድ ዓመት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ሲመለስ በርካታ ጨዋታዎችን ተከታትሎ ዘገባዎችን ለአንባቢ አቅርቧል። በአሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው እየተመራ ቤኒንን ከእዚያም ሱዳንን በመጨረሻ የማጣሪያ ጨዋታ በደርሶ መልስ ውጤት ዋልያዎቹ ድል አድርገው ወደ አፍሪካ ዋንጫ ሲመለሱ ጥቅምት 3ቀን 2005 ዓም ይዞት በወጣው እትሙ በፊት ገፁና በስፖርት ባለቀለም ገፁ የአሰልጣኞች፤ ተጫዋቾችና ደጋፊዎች ስሜትን የሚገልፁና በቃለ መጠይቅ የዳበሩ በርካታ ዘገባዎችን ማቅረብ ችሏል።